# ኢትዮ ቻምበር

ሚዲያ ጭማቂ

በኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት

በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የኮሚኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ ወርሃዊ

ሚያዚያ2014



ምክር ቤቱ ከሁለት ድርጅቶች ጋር ... 2

ተ/ዋና ፀኃፊው በኩባ ...2

ለኢኮኖሚያዊ ቀውሱና ለዋጋ...2

አስመጪዎች ለኮንቴይነሮች ይጠየቁ... 3

በዘጠኝ ወራት ውስጥ...3

የሲሚንቶ መሸጫ ዋጋን...3

በኢንዱስትሪው ዘርፍ ያሉ ..4

የራይድ ታክሲ አገልግሎት...4

የገቢዎች ሚኒስቴር በዘጠኝ...4

የውጭ ባለሀብቶች ኢትዮጵያ...4

ቁጥጥር የማይደረግበት የፍራንኮ...5

ለግሉ ዘርፍ እድገት የሚሆን...5

የአየር መንገዱ የጥገና ክፍል...5

የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ክለሳ...6

የዓለም ገንዘብ ድርጅት...6

ባንኮች ዕዳቸውን መክፈል...6

ከ3 ነጥብ 5 ቢሊየን ብር...6

አየር መንገዱ በኢትዮጵያና ቱርክ...7


## ምክር ቤቱ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጋር በመተባበር አገር አቀፍ ስልጠና እየሰጠ ነው

የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጋር በመተባበር አገር አቀፍ ስልጠና እየተካሄደ ነው

. 34ሺህ ሰልጣኞች ይሳተፋሉ

የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በአቅም ግንባታ እና ስልጠና ዘርፍ ላይ በትብብር ለመስራት የሚያስችላቸውን ግንኙነት እያጠናከሩ ሲሆን 35 ሺህ ሰልጣኞች የሚሳተፉበት ፤ በ33 የስልጠና ማዕከላት ላይ 94 አሰልጣኞች እና 20 የቢዝነስ ውጣውረድ ልምዶችን የሚያካፍሉ ተናጋዎች ከግንቦት 1-5 ቀን 2014 ዓም. በምክር ቤታችን ቻምበር አካዳሚ አስተባባሪነት በቅንጅት እየተካሄደ ይገኛል።

የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከመንግስት፣ ከንግዱ ማህበረሰብ፣ ከልማት አጋሮች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ንቁ የግል ዘርፍ እና ለንግድ ተስማሚ አካባቢን በመፍጠር ንግድ እና ኢንቨስትመንትን የማሳደግ፣ የአቅም ግንባታ ድጋፍ የመስጠት እና የምርምርና የአድቮኬሲ ሥራዎችን ያከናውናል።።።ከዚህ አንጻርም በተለይ የአቅም ግንባታ እና የስልጠና ፍላጎቶችን ለመመለስ ምክር ቤቱ የግሉን ዘርፍ የንግድ ሥራ ክህሎት በማሳደግ ከሌሎች የንግድ መሪዎች እና ከንግድ ማህበረሰቡ ጋር እንዲገናኙ ዕድሎችን ያመቻቻል፤ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከልም

- በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሥልጠና የመስጠት፣
- የቴክኒክ እና የክህሎት ስልጠናዎችን የማመቻቸት፣
- የንግድ ትምህርት ሴሚናሮችን የማዘጋጀት፣
- ከለጋሾች ድጋፍ በማፈላለግ ለአባላት ድጋፍ የመስጠት፣
- E-learning ፕሮግራም የማመቻቸት፣እንዲሁም
- የሥልጠናና የሰው ኃይል አቅርቦት ላይ ይሠራል፣

በሌላም በኩል የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የመንግሥትን የልማት የትኩረት አቅጣጫን መሠረት በማድረግ አዋጭ ለሆኑ እና ለተመረጡ የልማት ፕሮጀክቶች ከሀገር ውስጥና ከውጭ የብድር ገንዘብ በማሰባሰብ የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ ሚሰጥ ሲሆን ባንኩ ይህን ከፍተኛ ዋጋ ያለው ተልዕኮ እንዲሳካ ለቀጣይ አቅም ግንባታ፣ ለደንበኛ ተኮር አገልግሎትና ለአካባቢ ጥበቃ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል።

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የመንግስትን የትኩረት አቅጣጫን መሠረት በማድረግ ለሚቋቋሙ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃዎች ኪራይ /የሊዝ ፋይናንስ/ አገልግሎት እንዲሰጥ ከመንግሥት ከፍተኛ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። በዚህም መሠረት ባንኩ ኢንተርፕራይዞችን የካፒታል ዕቃ እንዲያገኙ ያመቻቻል።

የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ይህን ዓላማ ለመደገፍ የአቅም ግንባታ ስራውን በመወጣት ላይ ይገኛል።

## የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ተጠባባቂ ዋና ፀሀፊ የእስራኤል አምባሳደርን አነጋገሩ



የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ተጠባባቂ ዋና ፀሀፊ አቶ ውቤ መንግስቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የምክር ቤቱ የስራ ሃላፊዎች ጋር በመሆን በኢትዮጵያ የእስራኤል ኢምባሲ አምባሳደር አለልኝ አድማሱ የተመራውን የልዑካን ቡድን በፅ/ቤታቸው ተቀብለው ሁለቱ አገራት ያላቸውን የንግድና የኢኮኖሚ ግንኙነቶች በሚያጠናክሩበትና በትብብር በሚሰሩባቸው ጉዳዮች በተለይም የሁለትዮሽ ንግዱን ለማሻሻል ይረዳል ተብሎ የታቀደው የኢኮኖሚ ኮንፈረንስን በሚያዘጋጁበት ዙሪያ ሚያዚያ 21/2014 ዓ.ም ተወያዩ።

አምባሳደር አለልኝ እነደተናገሩት ከሰሞኑ የእስራኤል ኤሮስፔስ ኢንዱስትሪ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር በጋራ በይንግ የእቃ ጫኝ አውሮፕላንን በተሻሻለና በላቀ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ስምምነት ላይ የደረሱ መሆኑን በማስታወስ በቀጣይም በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የንግድ ግንኙት ለማጠናከር ተግተው እንደሚሰሩ አስምረውበታል። አያይዘውም የንግዱ ማህበረሰብ እርስ በርስ ግንኙነት የሚፈጥሩበት እና ስለ ሁለቱ አገራት የንግድና ኢንቨስትመንት እምቅ ሀብቶችና እድሎች በቂ መረጃና የእውቀት ልውውጥ የሚያገኙበት መድረክ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ ሊዘጋጅ የታቀደው የኢትዮ-እስራኤል የኢኮኖሚ ኮንፈረንስ ፋይዳው የጎላ ነው ብለዋል።

የምክር ቤቱ ተ/ዋና ፀሀፊ አቶ ውቤ በበኩላቸው ቀደም ሲል በኢምባሲው ግብዣ መሰረት ባደረጉት ውይይት ከሁለቱም ወገን የተውጣጣ ቴክኒካል ኮሚቴ ተቋቁሞ በእስራኤል እና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን የሁለትዮሽ ንግድ ማሻሻያ የኢኮኖሚ ኮንፈረንስ ለማካሄድ ዝርዝር እቅድ በጥሩ ሁኔታ እንደተዘጋጀ ገልፀዋል። በመቀጠልም ሊዘጋጅ የታሰበው ኮንፈረንስ ዋና አላማ በእስራኤል እና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን የሁለትዮሽ የንግድ ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር እንዲያስችል በዋነኝነት የአቻ ለአቻ የቢዝነስ ውይይት( business to business meeting) እና ነጋዴውን ከሸማቾች ጋር የሚያገናኝ ስብሰባን ( business to consumer meet-ing)፣ የሚያካትት እንዲሁም በሁለቱ ሀገራት የንግድ ምክር ቤቶች፣ አምራቾች፣ አከፋፋዮች እና ሌሎች የንግዱ ማህበረሰብ ክፍሎች መካከል በሚኖሩ የንግድ ግንኙነት ስምምነቶች ላይ ውይይት የሚደረግበት መድረክ ይሆናል ብለዋል። የኢትዮጵያ ቴሌኮምንና ትልልቅ ኩባንያዎችን ጨምሮ የቆዳ፣ የጨርቃጨርቅ፣ የእንጨት፣ የብረታብረትና ሌሎች ኢንተርፕራይዞች ምርቶቻቸውንና አገልግሎታቸውን የሚስተቀውቁበት እነዲሁም የተለያዩ አገሮች ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች የሚሳተፉበት በጎንዮሽም ክንቲባዎች፣ የፋይናንስ ተቋማት ሀላፊዎችና ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ሃላፊዎች ከንገዱ ማህበረሰብ ጋር የሚወያዩበት መድረኮች የሚዘጋጁበት 12ኛው የኢትዮ- ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒትን ምክር ቤቱ በግንቦት ወር መጨረሻ 2014 ዓ.ም የሚያካሂድ መሆኑን አብራርተው የእስራኤል ኩባንያዎችም በላቀ ቴክኖሎጂ የሚመረቱ ምርቶቻቸውንና አገልግሎታቸውን በዚሁ የንግድ ትርዒት ላይ ማስተዋቅ እንዲችሉ በሁለቱ አገሮች መካካል የሚዘጋጀው የኢኮኖሚ ኮንፈረንስ ንግድ ትርዒቱ በሚካሄድበት ወቅት (ከግንቦት 25-29 2014 ዓ.ም) ጎን ለጎን ቢካሄድ መልካም እንደሆነ ተናግረዋል። ተ/ዋና ፀሀፊው አክለውም ኢትዮጵያ ውስጥ የተሳማሩ የእስራኤል ኩባንያዎችም በንግድ ትርዒቱ ላይ ይሳተፉ ዘንድ በኢምባሲው በኩል መልእክት እንዲደርሳቸው ግብዣ አቅርበዋል።

## ምክር ቤቱ ከሁለት ድርጅቶች ጋር

የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት Afro Universal and General Trading PLC እና Eldix IT Technology PLC (360Ground) ከተባሉ ሁለት





ድርጅቶች ጋር ሚያዚያ 21/2014 ዓ.ም የውል ስምምነቶችን አደረገ፡፡

ምክር ቤቱ ከነዚህ ድርጅቶች ጋር የውል ስምምነቶችን የፈፀመው የኢ-ለርኒንግ (E-Learning )የመድረክ ንድፍና ልማት እና የኢ-ለርኒንግ ትምህርት መድረክ ሞጁል ዝግጅት ስራዎችን በጋራ ለመስራት ነው፡፡

## ተ/ዋና ፀኃፊው በኩባ የኢትዮጵያ



የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ተጠባባቂ ዋና ፀሀፊ አቶ ውቤ መንግስቱ ሚያዚያ 20 ቀን 2014 ዓ.ም. በኩባ የኢትዮጵያ አምባሳደር ዶክተር ገነት ተሾመን በፅ/ቤታቸዉ ተቀብለዉ አነጋገሩ፡፡

በኩባ አዲስ የተሾሙትን የኢትዮጵያ አምባሳደር ዶክተር ገነት ተሾመን መልካም የስራ ጊዜ እንዲሆንላቸው መልካም ምኞታቸውን የገለጹት የምክር ቤቱ ተ/ዋና ፀኃፊ አቶ ውቤ መንግስቱ፤ የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የግሉ ዘርፍ ድምፅ ተቋም እንደሆነና የአድቮኬሲና ምርምር፣ የአቅም ግንባታ እንዲሁም የንግድና ኢንቨስትመንት ማስፋፋት ስራዎችን እንደሚሰራ አብራርተዋል፡፡

በዚህ መነሻም የተለያዩ ንግድ እና ኢንቨስትመንትን ሊያሳድጉ በሚችሉ ዓለም ዓቀፍ የንግድ ትሪኢቶች፣ የቢዝነስ ፎረሞች፣ የቢዝነስ የአቻ-ለአቻ ውይይቶችን ከተለያዩ አገራት ጋር በትብብር በማዘጋጀት የአገራችን ምርቶች በስፋት እንዲተዋወቁ እና ገበያ እንዲያገኙ፣ የውጪ ኢንቨስትመንት(FDI) እንዲያድግ እየሰራ መሆኑን አንስተው ከኩባ ጋር የሚፈጠረው የንግድ እና ኢንቨስትመንት ትስስርም የዚሁ አካል እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

አምባሳደር ዶክተር ገነት ተሾመ በበኩላቸው በኢትዮጵያ እና ኩባ መካከል ያለው ወዳጅነት እጅግ ጠንካራ እና ለብዙ ዘመናት የቆየ መሆኑን እና ይህንንም አብሮነት ሁሉን አቀፍ ወደሆነ ፤ ስትራቴጂያዊ ትብብር ከፍ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አንስተው፤ በተለይም በንግድ እና ኢንቨስትመንት ዙሪያ ትብብራቸውን ለማሳደግ ስለሚቻልበት ሁኔታ ከኩባ በኩል ፍላጎት እንዳለ እና የሀቫና የንግድ ምክር ቤት ከኢትዮጵያ አቻው ጋር በጋራ ሊሰሩ በሚችሉባቸው መስኮች ዙሪያ የጋራ መግባቢያ ስምምነት ለመፈረም መዘጋጀቱን ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም በተለይም በእውቀት ሽግግር፣ በቴክኖሎጂ፣ በማምረቻ ፣ በጤናው ዘርፍ፣ ወዘተ ኩባ ያላትን ሰፊ እና የካበተ ልምድ እና ተመክሮ ለመጠቀም እንዲሁም ኢትዮጵያ ወደኩባ ልትልክ የምትችላቸው ምርቶችን በመለየት በጋራ ለመስራት እንደሚቻል አብራርተዋል፡፡

## ለኢኮኖሚያዊ ቀውሱና ለዋጋ ንረት መባባስ ዋና ምክንያት



የመሬት አቅርቦትና የአጠቃቀም መብት በከፍተኛ ደረጃ እያሽቆለቆለ መምጣት፣ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ በመድረሱ፣ ለዋጋ ንረትም ዋነኛ መንስዔ መሆኑን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ ባለሙያዎች ማኅበር ገለጸ፡፡

ማኅበሩ በወቅታዊ አገራዊ ኢኮኖሚ ጉዳዮች ዙሪያ ያጠናውን ጥናት ሰሞኑን ይፋ ባደረገበት ወቅት እንዳስታወቀው፣ የመሬት አስተዳደር በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ለተከሰተው ኢኮኖሚያዊ ቀውስና ለዋጋ ንረት መባባስ በዋናነት ተጠቃሽ ሆኗል፡፡

ለኢኮኖሚያዊ ቀውሱም ሆነ ለዋጋ ንረቱ መባባስ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም፣ ለሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች ቁልፍ ሚና ያለው የመሬት አቅርቦትና በመሬት መጠቀም መብት በከፍተኛ ሁኔታ መሸርሸሩ ከፍተኛ ጉዳት እያመጣ መሆኑንም ማኅበሩ ገልጿል፡፡ በሕጋዊ መንገድ መሬት አግኝቶ ማልማት ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ችግር እየሆነ መምጣቱን ባደረገው ጥናት ማረጋገጥ መቻሉን የገለጸው ማኅበሩ፣ ይህ ጉዳይ መፍትሔ ካላገኘም የሚያስከትለው ጉዳት የከፋ እንደሚሆን ጠቁሟል፡፡

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ ማኅበር የምርምርና የፖሊሲ ጥናት ዳይሬክተር ደግዬ ጎሹ (ዶ/ር)፣ ከመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር ከድጡ ወደ ማጡ እየሆነ መምጣቱን ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ በአግባቡ መሬት የማቅረብና የመጠቀም መብት እ.ኤ.አ. በ2013 ወደ 96 በመቶ አካባቢ የነበረ ቢሆንም፣ በ2021 ግን ወደ 21 በመቶ መውረዱን ማኅበሩ ያደረግኩት ባለው ጥናት ያመላክታል፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ ለግብርናም ሆነ ለማንኛውም ዓይነት ኢንቨስትመንት፣ እንዲሁም ለቤት ግንባታና በአጠቃላይ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ መሬትን በአግባቡ መጠቀም ተገቢ ቢሆንም፣ ይህንን ሀብት በአግባቡ መጠቀም ባለመቻሉ እያስከተለ ያለው ኢኮኖሚያዊ ችግር እየጨመረ እንዲሄድ አድርጎታል፡፡

ባለፉት 25 እና 30 ዓመታት የመሬት አቅርቦትና የመጠቀም መብት በከፍተኛ ሁኔታ እየወረደ መምጣት ደግሞ፣ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ጫና ከመፍጠር አልፎ፣ አሁን ለተከሰተው የኑሮ ውድነት ከፍተኛውን ድርሻ እንዲይዝ መደረጉም ተጠቅሷል፡፡ ማኅበሩ የችግሩን ግዝፈት ለማሳየት ሌላው የጠቀሰው አኃዛዊ መረጃ፣ እ.ኤ.አ. በ2017 ከ129 የዓለም አገሮች የመሬት አቅርቦትና የአጠቃቀም መብትን በተመለከተ የነበረው አፈጻጸም፣ ኢትዮጵያ 67ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣ የነበረ ቢሆንም፣ በ2021 ግን ወደ 115ኛ ደረጃ መውረዷ ተጠቁሟል፡፡

መሬትን በሕጋዊ መንገድ አግኝቶ ማልማት ከማይቻልበት ደረጃ መድረሱን የጠቆሙት ጎሽዬ (ዶ/ር)፣ በአሁኑ ወቅት መሬት ማግኘት የሚቻለው በሁለት መንገድ ብቻ ነው ብለዋል፡፡ ‹‹አንዱ መሬት ማግኛ ዘዴ ሙስና ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መሬትን በመውረር መውሰድ ነው፤›› ሲሉም አክለዋል፡፡ ይህም በሕጋዊ መንገድ መሬት ማግኘት ከባድ እንዲሆን አድርጎታል ብለዋል፡፡ አይደለም ለውጭ ኢንቨስተር ለአገር ውስጥም መሬት ማግኘት ከባድ እየሆነ መምጣቱን፣ በመሆኑም የመሬት አጠቃቀምና በመሬት የመጠቀም መብት እጅግ አሳሳቢ እየሆነ ስለመጣ ማሻሻያ ሊደረግበት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

‹‹ጉዳዩ መሬት የግል ይሁን ወይም የመንግሥት የሚለው ሳይሆን ባለው የመሬት ሥሪት እንኳን በአግባቡ ቢሠራ ለውጥ ሊመጣ ይችላል፤›› በማለት ትንታኔ የሰጡት ዳይሬክተሩ፣ እዚህ ጉዳይ ላይ መንግሥት በትኩረት ቢሠራ ኢኮኖሚውን በማሻሻል ብዙ ለውጦች ሊመጡ ይችላሉ የሚል እምነት አላቸው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ መሬትን በማቅረብና በመጠቀም ረገድ ያለው አፈጻጸም ከ96 በመቶ ወደ 21 በመቶ የወረደው፣ የመሬት ሥሪቱ ተቀይሮ ባለመሆኑ፣ መፍትሔ የሚሆነውም ባለው የመሬት ሥሪት በአግባቡ መሥራት መሆኑንም አክለዋል፡፡

መሬትን በአግባቡ መጠቀም ቢቻል የዋጋ ንረት በከፍተኛ ሁኔታ ሊቀንስ እንደሚችል የማኅበሩ ጥናት እንደሚያሳይ የገለጹት ጎሽዬ (ዶ/ር)፣ ችግሩ መዋቅራዊ መሆኑን ተቀብሎ በዚሁ አግባብ መፍታት ይገባል ብለዋል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ለኢንቨስትመንት፣ ለግብርና፣ ለቤት ግንባታም ሆነ ለመሳሰሉት መሬትን በሕጋዊ መንገድ መጠቀም የማይቻልበት ደረጃ ይደርሳል የሚል ሥጋት እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡

‹‹ኢትዮጵያ ግብርና መር ኢኮኖሚ ትከተላለች ሲባል ትልቁ መነሻ ሀብት ‹‹መሬትና ጉልበት ነው፤›› በማለት ያስታወሱት ጎሽዬ (ዶ/ር)፣ አሁን ግን ትልቁ የመሬት ሀብት ታንቆ እየመከነ መገኘቱ ጉዳት እያስከተለ ነው ብለዋል፡፡

‹‹ይህም በመሆኑ ግብርናው ኢኮኖሚውን መርቶ ሊነሳ ይቅርና አሁን ባለው ሁኔታ የዕለት እንጀራችንን ሊሰጠን ያልቻለበት ምክንያት፣ በመሬት ዙሪያ ያለውን ችግር መፍታት ባለመቻሉ ነው፤›› ሲሉ ጥናት አቅራቢው ገልጸዋል፡፡ በጥቅል ሲታይ ደግሞ፣ የመሬት አቅርቦትና መሬት ላይ እየታየ ያለው ችግር እየጨመረ የመጣውና ለችግሩ መባባስ መንግሥት በአብዛኛው መቆጣጠር ባለመቻሉ እንደሆነም ጥናቱ አሳይቷል ተብሏል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ባንኮች፣ ለተቀማጭ ገንዘብ በሚከፍሉት ወለድና በማበደሪያ ወለድ ምጣኔያቸው መካከል ያለው ልዩነት መጥበብ እንዳለበትም ማኅበሩ አሳስቧል፡፡

ባንኮች ለቁጠባ ገንዘብ የሚሰጡት ወለድ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ የዋጋ ንረቱን እንዳባባሰው፣ የማበደሪያ ወለዳቸውም የተመጣጠነ ባለመሆኑ ኢኮኖሚው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩንም ጠቁሟል፡፡

አሁን እንደሚታየው የኢትዮጵያ ባንኮች ጥሩ ትርፍ ከማግኘታቸውም በላይ ዕድገት እያሳዩ ቢሆንም፣ እያገኙ ያሉት ከፍተኛ ትርፍ በማበደሪያና በብድር ወለድ ምጣኔ መካከል ያለውን ከፍተኛ ልዩነት እየተጠቀሙ በመሆኑ፣ ለዋጋ ንረት ምክንያት ሆኗል ተብሏል፡፡ ለተቀማጭ ገንዘብ የሚታሰበው ወለድና የማበደሪያ ወለድ መካከል ያለው ልዩነት በጣም እየሰፋ መሄዱ፣ ባንኮችን ከመጠበቅ ሌላ ምንም ፋይዳ እንደሌለው የሚጠቁመው

# አስመጪዎች ለኮንቴይነሮች ይጠየቁ የነበረው የዋስትና መያዣ

የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ከወደብ ወደ ግል መጋዘኖች ለማጓጓዝ፣ በኮንቴይነር ያስከፍል የነበረውን የዋስትና ገንዘብ፣ ከሰባት እጥፍ በላይ በ700 በመቶ በማሳደግ ለአንድ ባለ 40 ፊት ኮንቴይነር 200 ሺሕ ብር ማስያዣ እንደሚጠይቅ አስታወቀ።

ድርጅቱ የኮንቴይነር ማስያዣን በተመለከተ ሚያዚያ 4 ቀን 2014 ዓ.ም. ባወጣው አጭር የጽሑፍ ማስታወቂያ፣ መደበኛ ለሆኑ ባለ 20 ጫማ ኮንቴይነሮች፣ 100 ሺሕ ብር፣ ለ40 ጫማ ኮንቴነሮች ደግሞ 200 ሺሕ ብር ማስያዣ የሚጠይቅ መሆኑን አስታውቋል።

መደበኛ ላልሆኑትና በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ምርቶችን የሚይዙ ወይም ማቀዝቀዣ ላላቸው ኮንቴይነሮች ደግሞ፣ ለ20 ጫማ ኮንቴይነር 120 ሺሕ ብር፣ ለ40 ጫማ ኮንቴይነር ደግሞ 240 ሺሕ ብር ማስያዣ እንደሚያስከፍል አስታውቋል።

ድርጅቱ ለኮንቴነሮች ይጠይቅ በነበረው የዋስትና ማስያዣ ገንዘብ ላይ ያደረገው የዋጋ ጭማሪ በእጅጉ የተጋነነ፣ አስመጪዎችን ላልተገባ የመንቀሳቀሻ ገንዘብ ፍላጎት የሚዳርግ መሆኑን የድርጅቱ ደንበኞች በመጠቆም ቅሬታቸውን አሰምተዋል።

ከዚህ ቀደም ድርጅቱ ለባለ 20 ጫማ ኮንቴይነር ይጠይቅ የነበረው የማስያዣ ገንዘብ መጠን 15 ሺሕ ብር ሲሆን፣ ለባለ 40 ፊት ኮንቴይነር ደግሞ 25 ሺሕ ብር ይጠይቅ እንደነበር አስመጪዎች ለሪፖርተር ገልጸዋል።

አንድን ኮንቴይነር ተጠቅሞ ለመመለስ ይህንን ያህል ዋጋ የተጠየቀበት ምክንያት ግልጽ ባይሆንም፣ እንዲህ ያሉ ጭማሪዎች የዋጋ ንረቱን ያባብሳሉ ሲሉ ሪፖርተር ያነጋገራቸው ደንበኞች ቅሬታቸውን ገልጸዋል።

በአጠቃላይ የንግድ ሒደቱ ላይ ከፍተኛ ጫና እንደሚፈጥር የጠቆሙት አስመጪዎች፣ የድርጅቱን የተጋነነ የኮንቴይነር መያዣ ዋጋ ጭማሪ ተቃውመዋል።

በአሁኑ ወቅት ለማጓጓዣና ከዚሁ ጋር ለተያያዙ አገልግሎቶች የሚጠየቁ ክፍያዎች እጅግ ከፍተኛ ጭማሪ እየተደረገባቸው መምጣቱ፣ በአገሪቱ ላለው ከፍተኛ የዋጋ ንረት አንዱ አባባሽ ምክንያት መሆኑን አስመጪዎቹ ተናግረዋል።

ስሜ አይጠቀስ ያሉ የድርጀቱ ደንበኛ ለሪፖርተር እንደገለጹት፣ ‹‹ይህ ማስታወቂያ ከወጣ በኋላ አሥር ኮንቴይነሮች ከወደብ ማስነሳት ያለባቸው አስመጪዎች ለኮንቴይነሮቹ ማስያዣ ብቻ ሁለት ሚሊዮን ብር ተጠይቀዋል። ቀድሞ በነበረው አሠራር ግን ይጠየቅ የነረው 150 ሺሕ ብር ከመሆኑ አንፃር ሲታይ ይህ ጭማሪ እጅግ ከፍተኛ የሚባል ነው፤›› ብለዋል።

ለኮንቴይነር ማስያዣ የሚከፈለውን ገንዘብ አስመጪዎች የሚያገኙት በባንክ ብድር እንደሆነ፣ የተከፈለውን ማስያዣ ገንዘብ ለማስመለስ ደግሞ አስከ አራት ወራት የሚፈጅ በመሆኑ የዋጋ ንረት መባባስን ማስከተሉ እንደማይቀር ገልጸዋል።

‹‹በኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ የገንዘብ እጥረት ባለበት ሁኔታ እንዲህ ያለውን አሠራር መተግበር ችግሩን ያብሰዋል፤›› የሚሉት እኚሁ አስተያየት ሰጪ፣ ድርጅቱ ውሳኔውን ሊያጤን እንደሚገባም አሳስበዋል።

ይህንን ችግር የበለጠ የሚያጎላው ደግሞ በአሁኑ ወቅት ከሎጂስቲክስ ጋር በተያያዘ እየታየ ያለው የዋጋ ጭማሪ ከፍተኛ እየሆነ በመምጣቱ ነው።

ከሎጂስቲክስ ጋር በተያያዘ አብዛኛውን ሥራ የሚሠራው የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት መሆኑን የሚጠቅሱት ሪፖርተር ያነጋገራቸው አስመጪ፣ ድርጅቱ በኮንቴይነር ዕቃ አስጭኖ ለማምጣት አሁን የሚጠየቀው ዋጋ እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ ገልጸዋል።

ለአብነትም ከቻይና እስከ ጂቡቲ ወደብ ድረስ አንድ ኮንቴይነር ዕቃ አስጭኖ ለመምጣት ቀደም ሲል ይከፈል የነበረው ዋጋ አሁን ከአራት እስከ አምስት እጥፍ መጨመሩን በመጥቀስ፣ የዋጋ ንረትን ሊያብስ የሚችል ጭማሪ ማድረግ ተገቢ እንዳልሆነ ገልጸዋል።

ከአንድ ዓመት በፊት ከዱባይ እስከ ጂቡቲ ወደብ ድረስ አንድ ኮንቴይነር ዕቃ ለማጓጓዝ እስከ 2,200 ዶላር ይጠየቅ እንደነበረ ያስታወሱት አስመጪው፣ አሁን ግን እስከ 5,200 ዶላር እንደሚከፈልበት አስረድተዋል።

# በዘጠኝ ወራት ውስጥ 26 አምራች ፋብሪካዎች መዘጋታቸው ተገለጸ

በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት የምርት ግብዓት ከውጭ አስመጥተው ማምረት ያልቻሉ 26 የኤሌክትሮኒክና የማሽነሪ ፋብሪካዎች በዘጠኝ ወራት ጊዜ ወስጥ መዘጋታቸው ተገለጸ።

በጋራ ከታቀፉት የአውቶሞቲቭና ፋብሪኬሽን፣ ኤሌክትሪካል፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ ማሽሪና ኢኪዩፕመንት ዘርፎች ወስጥ ወደ ውጭ የሚላከውን ምርት ከፍተኛ ድርሻ የሚይዙት ኤክትሮኒክ ኩባንያዎች በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት እጅጉን እየተፈተኑ መሆኑን የማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ምርመራና ልማት ማዕከል አስታውቋል። የማዕከሉ ኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር ፊጤ በቀለ ለሪፖርተር እንደተናገሩት ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ 19.3 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጡ የኢንጂነሪንግ፣ ኤሌክትሪካልና ኤሌክትሮኒካል ምርቶች ወደ ውጭ የተላኩ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙት ኤሌክትሮኒካል ምርቶች ናቸው።

እንደ የፓወር ኬብል፣ ትራንስፎርመን፣ የቴሌኮሙዩኒኬሽን ኬብል (ኤሌክትሪካል) ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ፍሪጅና ሞባይል (ኤሌክትሮኒክስ) ያሉ ምርቶችን የሚያመተርቱት እነዚህ ፋብሪካዎች፣ ምርቶቻቸው የሚላከው ለኬንያ፣ ሩዋንዳና ሌሎች  የአፍሪካ አገሮች ነው። ይሁንና በአገሪቱ ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ የማኑፋክቸሪንግ ፋብሪካዎች ፈተና የሆነው የውጭ ምንዛሪ እጥረት 26 የኤሌክትሮኒክስና የአውቶሞቲቭ ፋብሪካዎች ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ እንዲዘጉ ማድረጉን አቶ ፊጤ አስረድተዋል።

ብሔራዊ ባንክ ከወራት በፊት ባወጣው የውጭ ምንዛሪ ድልድል መሠረት የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ቅድሚያ ተሰጥቶት እንደነበር ያስታወሱት ዳይሬክተሩ፣ የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ አቅም ዝቅተኛ መሆኑ ፋብሪካዎቹ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ እንዳደረጋቸው አስረድተዋል። የውጭ ምንዛሪ የተመደበላቸው ፋብሪካዎች ጋርም ቢሆን መጓተት እንደሚታይ አክለዋል። ከዚህም ባሻገር ፋብሪካዎቹ የኃይል መቆራረጥ፣ የፋይናንስ አቅም እጥረትና የመሥሪያ ቦታ ችግር እንቅፋት እንደሆኑባቸውም ተናግረዋል።

በዚህም ሳቢያ በማምረት ላይ የሚገኙት ፋብሪካዎችም ቢሆኑ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ያመረቱት ከአቅማቸው 19.26 በመቶውን ብቻ ተጠቅመው ነው።

ኤሌክትሮኒክ ዘርፉን ጨምሮ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ዘርፍ በዘጠኝ ወራት ውስጥ 31.9 ቢሊዮን ብር ዋጋ ያለው ምርት ማምረታ መቻሉን

# የሲሚንቶ መሸጫ ዋጋን የሚቆጣጠር የግብይት መመርያ በድጋሚ

መንግሥት በሰው ሠራሽ ምክንያቶች የሚፈጠረውን የሲሚንቶ እጥረት ለመቅረፍ በማለት ነሐሴ 2012 ዓ.ም. ያወጣውን የሲሚንቶ ግብይት መመርያ፣ ከአንድ ዓመት ቆይታ በኋላ በሐምሌ ወር 2013 ዓ.ም. በመሻር በድጋሚ የሲሚንቶ ግብይት መመርያ እያዘጋጀ መሆኑ ተገለጸ። መመርያውን እያዘጋጀ ያለው ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሲሚንቶ ሽያጭ የሚከናወንበት የነፃ ገበያ ሥርዓት ለቁጥጥር አመቺ ባለመሆኑ፣ የትርፍ ህዳግን በመወሰን የመሸጫ ዋጋ ላይ ቁጥጥር ለማድረግ ማሰቡን አስታውቋል።

ነጋዴዎች በሚፈጥሯቸው የተለያዩ ዘዴዎች ምክንያት የሲሚንቶ ግብይትን በሚፈለገው ሁኔታ መቆጣጠር አለመቻሉን ለሪፖርተት የተናገሩት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሀሰን መሐመድ፣ ችግሩን ለመፍታት የተለያዩ ዕርምጃዎች ቢወሰዱም ውጤታማ እንዳልሆኑ ገልጸዋል። አቶ ሀሰን ሲሚንቶ አንድ ሺሕ ብር እየተሸጠ መሆኑ ቢታወቅም፣ ሚኒስቴሩ ቁጥጥር ሲያደርግ ገበያው ውስጥ  የሚያገኘው ደረሰኝ 600 እና 700 ብር የተሸጠበትን መሆኑን በማሳያነት አውስተዋል።

በዚህም ምክንያት ሚኒስቴሩ የሲሚንቶ ሥርጭትንና የትርፍ ህዳግን በመወሰን የመሸጫ ዋጋን የሚቆጣጠር መመርያ አዘጋጅቶ እያጠናቀቀ መሆኑን፣ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥም ለማክሮ ኢኮኖሚክ ኮሚቴ እንደሚያቀርብ አስታውቀዋል።

እንደ ሌሎች የግንባታ ግብዓቶች ሁሉ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ የታየበት ሲሚንቶ በገበያው ላይ ካለመገኘቱም ባሻገር፣ በኩንታል 1,100 ብር ገደማ ሲሸጥ ሰንብቷል። የሲሚንቶ ገበያው ውስብስብ የሆኑ ችግሮች፣ ረዣዥም እጆችና ብልሹ አሠራር ያለበት መሆኑን ለሪፖርተር ያስረዱት አቶ ሀሰን፣ አሁን ግን የአቅርቦትና የፍላጎት አለመመጣጠኑ ለዋጋ ንረት ዋነኛ ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ‹‹ሲሚንቶ የሚከዝኑ (የሚሸሽጉ) ነጋዴዎች ሊኖሩ ይችላል›› በሚል ዕሳቤ ባለፉት ሁለት ሳምንታት ከአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ፣ ከፌዴራል ፖሊስ፣ ከአዲስ አበባ ፖሊስ፣ ከብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ጋር በመሆን ያደረገው ኦፕሬሽን እንዳልተሳካ ተናግረዋል። ይህም ችግሩ የምርት እጥረት መሆኑን እንዳሳየና አብዛኞቹ ፋብሪካዎች በፀጥታ ምክንያት ምርት ማቆማቸው እጥረት እንዲከሰት ማድረጉን አክለዋል።

የምርት እጥረት በተፈጥሮ ወደ ዋጋ ጭማሪ እንደሚመራ ያስረዱት ሚኒስትር ዴኤታው፣ ሲሚንቶ እንደ ዘይት፣ ስኳርና ስንዴ መሠረታዊ ሸቀጥ ታይቶ በሚኒስቴሩ የትርፍ ህዳግ እንዲወጣለት ጥያቄ እንደሚቀርብ ተናግረዋል።

አሁን ባለው ውሳኔ ሚኒስቴሩ እያዘጋጀ ያለው የትርፍ ህዳግ ጅምላና ችርቻሮ ነጋዴዎች ላይ ያነጣጠረ መሆኑን የተናገሩት አቶ ሀሰን፣ ፋብሪካዎች ሲሚንቶውን የሚሸጡበት ዋጋ ተመጣጣኝ መሆኑን አስረድተዋል። ይሁንና ሚኒስቴሩ ከሚመለከተው የመንግሥት ተቋም ጋር ተነጋግሮ በፋብሪካዎቹ ላይ የሚያጣራው ጉዳይ እንዳለ፣ ማጣራት ተደርጎም የትርፍ ህዳጉ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል።

በተጨማሪም እየወጣ ያለው የግብይት መመርያ የሲሚንቶ ምርት ሥርጭትን ለመቆጣጠር እንደሚያገለግል፣ ሲሚንቶ ከምርት እስከ ሽያጭ ሒደቱ ክትትል እንደሚደረግበት አስታውቀዋል። እንደ አቶ ሀሰን ገለጻ፣ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመሆን ሁሉም መሠረታዊ ሸቀጦች ላይ ሥርጭት ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ዲጂታል ሥርዓት እያዘጋጀ ነው። ዲጂታል ሥርዓቱ ተግባራዊ ሲሆን ምርቱ ለማንና የት እንደሸጠ የሚታይ በመሆኑ ሚኒስቴሩ የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት፣ የፌዴራል ፖሊስና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በጋራ ክትትል ማድረግ እንደሚችሉ አስረድተዋል።

የቀድሞው ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሲሚንቶ ከፋብሪካዎች ወደ ተጠቃሚዎች የሚደርስበት የግብይትና ሥርጭት ሒደት ከፍተኛ ችግር ያለበት እንደሆነ በመግለጽ፣ ነሐሴ 2012 ዓ.ም. ያወጣውን የሲሚንቶ ግብይት መመርያ ያነሳው ከአንድ ዓመት በኋላ ነበር። ሚኒስቴሩ መመርያውን ሲሽር የክረምት ወቅት በመሆኑ የፍላጎት ማነስ የሚከሰት መሆኑን፣ አምራች ኢንዱስትሪዎች አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች

# በኢንዱስትሪው ዘርፍ ያሉ ችግሮችን



“ኢትዮጵያ ታምርት” በሚል ሀገራዊ ንቅናቄ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ምርታማነት ለማሳደግ እና በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት እየተሠራ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

የሀገራዊ ንቅናቄ ዋና ዓላማም የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ችግሮች መፍታት፣ ለዘርፉ ዘላቂ ልማትና ተወዳዳሪነት ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እንዲሁም ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግሩ ዘርፉ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማስቻል ነው ተብሏል፡፡

በንቅናቄው የውጤታማ ሀገራት ተሞክሮ ተቀምሮበት የአምራች ኢንዱስትሪውን ምርታማነት በማሳደግ ተወዳዳሪ እና ውጤታማ እንዲሆን እየተሠራ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስትር መላኩ አለበል ተናግረዋል፡፡

ለአምራች ኢንዱስትሪው ትኩረት በመስጠት አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን በመሳብ፣ ነባሮቹን በማጠናከር ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የተሻለ ምጣኔሃብት ለመገንባትም እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ከአምራች ኢንዱስትሪው ምርት ለውጪ ገበያ በማቅረብ 390 ሚሊየን ዶላር ገቢ የተገኘ ሲሆን ይህም የእቅዱን 87 በመቶ መፈፀሙን አመላክተዋል፡፡

በዘርፉ ያሉ ችግሮችን መቅረፍ እና ምቹ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ሀገሪቷ ከዘርፉ የምታገኘውን ገቢ ለማሳደግ የሚመለከታቸው አካላት በትጋት ሊሠሩ ይገባልም ብለዋል፡፡

የፌዴራል እና የክልል ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በደብረ ብርሃን ከተማ የሚገኙ ነባር ኢንቨስትመንቶችን መጎብኘታቸውን ከሚኒስቴሩ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

https://waltainfo.com/am/በኢንዱስትሪው-ዘርፍ-ያሉ-ች34565/

# የራይድ ታክሲ አገልግሎት ታሪፍ በመንግሥት የማይተመን ከሆነ የነዳጅ

በተለምዶ ራይድ ወይም የሳሎን ታክሲ አገልግሎት ሰጪዎች የሚያስከፍሉት ታሪፍ በመንግሥት የማይወሰን ከሆነ የነዳጅ ድጎማ ተጠቃሚ እንደማይሆኑ ተጠቆመ፡፡

ለሕዝብ ፋይዳ ካላቸው የትራንስፖርት ሰጪዎች በስተቀር፣ ለሁሉም ተሽከርካሪዎች የሚነሳው የነዳጅ ድጎማ ከሁለት ወራት ተኩል በኋላ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን፣ ከዚያም የነዳጅ ዋጋ በዓለም አቀፍ ገበያው የሚተመን ይሆናል፡፡

የታለመ የነዳጅ ዋጋ ድጎማ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን፣ በተመረጡ የትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የሚውል፣ በጊዜ የተገደበ ድጋፍ እንደሆነ በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀው የውሳኔ ሐሳብ ያሳያል፡፡

የአዲሱን አሠራር ሒደት የሚተነትነው የውሳኔ ሐሳብ የማዘጋጀት ሒደቱ ላይ የተሳተፉና ስማቸው እንዳይገለጽ የጠየቁ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሥራ ኃላፊ ለሪፖርተር እንደገለጹት፣ የነዳጅ ድጎማው በተመረጡ ተሽከርካሪዎች ላይ መተግበር ያስፈለገው የመንግሥት ወጪ ለመቀነስና አነስተኛ ገቢ ያላቸውን ዜጎች ለመርዳት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የሥራ ኃላፊው ለሪፖርተር እንደተናገሩት ከመንግሥት ሥምሪት ውጭ የሆኑ ታሪፋቸውም በገበያ የሚመራ ተሽከርካሪዎች የድጎማው አካል የማይሆኑ ሲሆን፣ ይህም ምንም እንኳን መካከለኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች ላይ መጠነኛ ጫና ያሳድራል የሚል ፍራቻ ቢጭርም አስፈላጊ ውሳኔ መሆኑን አክለዋል፡፡

ሪፖርተር ከውሳኔ ሐሳብ መረዳት እንደቻለው ድጎማው ሲነሳ የዓለም ነዳጅ ውጤቶች ገበያ ሁኔታን ያገናዘበ የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ማስተካከያ የሚደረግ ሲሆን፣ ይህም ከአምስት ዓመታት ላልበለጠ ጊዜ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

በውሳኔው መሠረት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በሚሆን ታሪፍና ሥምሪት ለመሥራት ከተስማሙ የትራንስፖርት ሰጪዎች በተጨማሪ፣ በማኅበር ታቅፈው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎቶች የሚሰጡ አሽከርካሪዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ባለሦስት እግር ተሽከርካሪዎች፣ ኮድ 1 እና 3 ሚኒባሶች፣ የከተማ አውቶብሶች፣ አገር አቋራጭ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችና የመጫን አቅማቸው እስከ 47 የሆኑ የሕዝብ ትራንስፖርት ሰጪዎች የድጎማው ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

የሳሎን ታክሲ አገልግሎት ሰጪዎች መካከል የሆነው የዛይ ራይድ መሥራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ ሀብታሙ ታደሰ፣ ድጎማው መሰል አገልግሎት ሰጪዎችን ባለማካተቱ ቅር እንደተሰኙ የተናገሩ ሲሆን፣ የትራንስፖርት እጥረትን ሊያባብስ እንደሚችል አስጠንቅቀዋል፡፡

አቶ ሀብታሙ እንደተናገሩት የትራንስፖርት እጥረት ሳይቀረፍ የራይድ ታክሲ አገልግሎት ከድጎማው ተጠቃሚ እንዳይሆን ማድረግ ያለውን ችግር ከማባባስ ባሻገር በዚህ አገልግሎት ሰጪዎች የሚሰበሰበውን የታክስ መጠን ሊቀንሰው እንደሚችልና የዘርፉን ዕድገት ሊያቀጭጨው እንደሚችል ሥጋታቸውን ለሪፖርተር አጋርተዋል፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት ከ40 በላይ የሳሎን ታክሲ አገልግሎት ሰጪዎች ገበያውን የተቀላቀሉ ሲሆን፣ ከ30 ሺሕ በላይ ተሽከርካሪዎች በሥራቸው አቅፈዋል ተብሎ ይገመታል፡፡ በአሁን ወቅት በአማካይ አሥር ብር በኪሎ

# የገቢዎች ሚኒስቴር በዘጠኝ ወራት ውስጥ የዕቅዱን 93

የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ከ200 በላይ ሠራተኞች ላይ ዕርምጃ ወሰድኩ ብሏል

በተያዘው ዓመት መጨረሻ 360 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ አንዳቀደ ያስታወቀው የገቢዎች ሚኒስቴር፣ ባለፉት ዘጠኝ ወራት የሰበሰበው ገቢ የዕቅዱን 93 ከመቶ እንደሚሸፍን አስታወቀ፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ የተሰበሰበው ገቢ ከ248.6 ቢሊዮን ብር በላይ እንደሆነ ያስታወቀ ሲሆን፣ ይህም ለመሰብሰብ ካቀደው 267.5 ቢሊዮን ብር በ18.9 ቢሊዮን ብር ያነሰ ነው፡፡ ነገር ግን የተሰበሰበው ገቢ ከወር በፊት በስምንት ወራት ውስጥ ከተሰበሰው 221.4 ቢሊዮን ብር ገቢ በ27.1 ቢሊዮን ብልጫ የተገኘበት እንደሆነ ታውቋል፡፡

የመጋቢት ወር ጨምሮ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ከተሰበሰበው ገቢ ከአገር ውስጥ ታክስ የተሰበሰበው 145.2 ቢሊዮን ብር ሲሆን፣ ከወጪ ንግድ ቀረጥና ታክስ የተሰበሰበው ገቢ ደግሞ 103.3 ቢሊዮን ብር ሆኗል፡፡

በአገሪቱ ውስጥ በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ምክንያት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሥር የሚገኙ አራት ገቢ ሰብሳቢ ቅርንጫፎች ከሥራ ውጪ እንደሆኑበት ያስታወሰው የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የተለመደው የንግድ ሥርዓት እንቅስቃሴ በተቀዛቀዘበት ወቅት የተሰበሰበ ገቢ በመሆኑ አፈጻጸሙ አበረታች እንደሆነ አስታውቋል፡፡

የገቢዎች ሚኒስቴር በተያዘው ዓመት ከአገር ውስጥ ታክስ ብቻ 205 ቢሊዮን ብር እንደሚሰበሰብ ግብ የተቀመጠ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ 154.7 ብር፣ እንዲሁም ከሎተሪ ትርፍ 204.9 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ እንደታቀደ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አስታውቋል፡፡

ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ በመቀሌ ገቢዎችና ሚኒስቴር ጉምሩክ ኮሚሽን ቅርንጫፎች በተያዘው ዓመት የመጀመርያዎቹ አምስት ወራት ብቻ በድምሩ 1.8 ቢሊየን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ ምንም ገቢ እንዳልተሰበሰበ ከዚህ ቀደም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አስታውቆ የነበረ ሲሆን፣ በተመሳሳይ በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ኮሚሽን ቅርንጫፎች በአምስት ወራቱ ውስጥ ለመሰብሰብ ታቅዶ ከነበረው 2.3 ቢሊየን ብር የተሰበሰበው 1.9 ቢሊዮን ብር ብቻ እንደነበረ ተገልጿል፡፡ በዚህም በተጠቀሱት ወራት ውስጥ ከመቀሌና ኮምቦልቻ አራት ቅርንጫፎች ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው 3.3 ቢሊየን ብር ውስጥ፣ 1.9 ቢሊየን ብር ብቻ እንደተሰበሰበ መገለጹ የሚታወስ ሲሆን፣ 2.3 ቢሊየን ብር ሳይሰበሰብ ቀርቷል፡፡

በሌላ በኩል የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ከ43 ቢሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን ያስታወቀ ሲሆን፣ ይህም ቢሮው በዘጠኙ ወራት ውስጥ ለመሰብሰብ ካቀደው 37 ቢሊዮን ብር የስድስት ቢሊዮን ብር ብልጫ የታየበት እንደሆነ ገልጿል፡፡

# የውጭ ባለሀብቶች ኢትዮጵያ ውስጥ የምርምር ሥራና ሽያጭ ላይ እንዲሰማሩ ተፈቀደ

ከአሥር ዓመታት በኋላ ተሻሽሎ የፀደቀው የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ፣ የውጭ ባለሀብቶች ኢትዮጵያ ውስጥ የምርምር ሥራና ሽያጭን በቢዝነስ መልክ እንዲያካሂዱ ፈቀደ፡፡ ፖሊሲው የአገር ውስጥ የግል ባለሀብቶች በዘርፉ ላይ እንዲሰማሩ የማበረታቻ ሥርዓት የመዘርጋት ዓላማም ይዟል፡፡

የሚኒስትሮች ምክር ቤት መጋቢት 17 ቀን 2014 ዓ.ም. ባካሄደው 6ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ የፀደቀው የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ፣ በሥሩ ከያዛቸው ስምንት ቁልፍ የትኩረት መስኮች ውስጥ አንዱ ምርምርና ልማት የሚለው ነው፡፡ ፖሊሲው በመንግሥትም ሆነ በግል ሴክተሩ እምብዛም ትኩረት ያልተሰጠውን የምርምር ዘርፍ ለማነቃቃት ማሰቡን ለሪፖርተር የተናገሩት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትሩ ስትራቴጂካዊ አማካሪ አቶ ሔኖክ አህመድ፣ ፖሊሲው የምርምር ውጤቶች ኢኮኖሚያዊ ዋጋ እንዲኖራቸው ሥርዓት እንደሚዘረጋ አስረድተዋል፡፡

አቶ ሔኖክ ከዚህ ቀደም የምርምር ዘርፉ ለመንግሥት ብቻ የተተወ እንደነበር አስታውሰው፣ የግሉ ዘርፍ የምርምር ውጤቶችን ለመሸጥ ቢፈልግ እንኳን፣ የንግድ ሕጉ የምርምር ሥራ ሽያጭን እንደ አንድ የንግድ ዘርፍ ዕውቅና እንዳልሰጠው ገልጸዋል፡፡ አሁን በፀደቀው ፖሊሲ መሠረት ግን፣ የግል ዘርፎችም ሆኑ የውጭ ኩባንያዎች የምርምር ውጤቶችንና በምርምር የተገኙ መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች መሸጥ ይችላሉ፡፡

እንደ አዲስ የሚቋቋሙ ኩባንያዎች የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ እንደሚሆኑ፣ አዳዲስ ኩባንያዎች ሲቋቋሙ የሚገቡበት ዘርፍ ውስጥ ያለው ሁኔታ ምን ይመስላል የሚለውን በራሳቸው ከማጥናት ይልቅ፣ ለዚህ ተብለው የተቋቋሙ ተቋማት ያደረጓቸውን ጥናቶች መግዛት እንደሚችሉ አስረድተዋል፡፡ አንድ ምርት በደንበኞች ዘንድ ያለው ተጠቃሚነት ምን ያህል ነው? ደንበኞች ምን ይፈልጋሉ? የገበያ ትስስሩ ምን ያመስላል? እንዲሁም በዘርፉ ላይ ያሉ ተወዳዳሪዎች ተደራሽነታቸው ምን ያህል ነው የሚሉትን መረጃዎች ምርምር ከሚያደርጉት ተቋማት ይገዛሉ ብለዋል፡፡

ምርምር አድርገው የሚሸጡ ተቋማት ሥራቸው ከኢትዮጵያም ውጪ በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚሸጥበት ዕድል እንደሚኖር አክለዋል፡፡ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ደግሞ በዚህ ዘርፍ ላይ እንዲሰማሩ የተለያዩ ማበረታቻዎች ይቀርቡላቸዋል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

እንዲህ ዓይነት ጥናቶች ሲደረጉ የቆዩት በመንግሥት ብቻ መሆኑን የሚናገሩት አቶ ሔኖክ፣ አንዳንድ ሰዎች ከሚያደርጓቸው በጣም ትናንሽ የሚባሉ ምርምሮች ውጪ የግሉ ዘርፍ እንዳልተሰማራበት ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ዘርፉ የተደራጀ ሥርዓት ስላልተፈጠረለት ቁጥጥር እየተደረገበት፣ ዕውቅና እየተሰጠው የሚንቀሳቀስ እንዳልነበረ አክለዋል፡፡ አሁን ግን ሚኒስቴሩ ይኼንን ሥርዓት የማምጣት፣ አገራዊ ምርምሮችን የመምራትና የመቆጣጠር ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ኢንዱስትሪዎች ምርትና አገልግሎታቸው በጥናት ላይ ያልተመሠረተ በመሆኑ በዓለም አቀፍ ገበያ ውስጥ እንዲሳተፉ እንደማያግዳቸው የሚያወሱት አማካሪው፣ አሁን የፀደቀው ፖሊሲ ኢንዱስትሪዎች ጥናትና ምርምርን አንድ የሥራ ክፍላቸው የሚያደርጉበትን ሥርዓት እንደሚዘረጋ ተናግረዋል፡፡ ይኼንን ፖሊሲ የሚያወርድ አዋጅ እንዲሁም ማስፈጸሚያ ደንብና መመርያ እንደሚወጣለት ተገልጿል፡፡

## ቁጥጥር የማይደረግበት የፍራንኮ ቫሉታ ንግድ መዘዞች

መንግሥት በመሠረታዊ የፍጆታ ሸቀጣ ሸቀጦች ላይ የሚታየውን የአቅርቦትና የፍላጎት አለመጣጣም ለማጥበብና የውጭ ምንዛሪ እጥረት የፈጠረውን ጫና በመጠኑ ለማቅለል በማሰብ, የፍራንኮ ቫሉታ ንግድን መፍቀዱ ይታወሳል።

ይህንን ተከትሎም በመደበኛው የውጭ ምንዛሪ ገበያና በጥቁር ገበያው መካከል የነበረው የዶላር መግዣ ዋጋ በከፍተኛ ምጣኔ ማሻቀቡ እየተስተዋለ ነው።

መንግሥት የፍራንኮ ቫሉታ የንግድ ዕድልን በፈቀደበት ወቅት አንድ የአሜሪካን ዶላር በመደበኛው የውጭ ምንዛሪ ገበያ ላይ ይሸጥ የነበረው 52 ብር ገደማ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ወቅት በጥቁር ገበያው የነበረው የአንድ ዶላር ዋጋ 63 ብር ገደማ እንደነበር ሪፖርተር የሰበሰባቸው መረጃዎች ያመለክታሉ።

በመደበኛው የውጭ ምንዛሪ ገበያ የአንድ ዶላር መሸጫ ዋጋ በአነተስተኛ ምጣኔ ጨመሩን ቢቀጥልም፣ በአሁኑ ወቅት ያለው የመሸጫ ዋጋ ከ52 ብር ዘሎ አልሄደም። ይሁን እንጂ የፍራንኮ ቫሉታ ንግድ መፈቀዱን ተከትሎ የጥቁር ገበያው የመሸጫ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ እያሻቀበ በመሄድ በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ አንድ ዶላር ከ70 ብር እስከ 71 ብር በመሸጥ ላይ መሆኑን ሪፖርተር ማረጋገጥ ችሏል።

ከዚህም ባለፈ ሕገወጥ የዶላር ዝውውር በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ሲሆን፣ በጉምሩክ ኮሚሽንና በፌዴራል ፖሊስ ሰሞኑን በሕገወጥ መንገድ ከአገር ሊወጡ ሲሉ የተያዙ የውጭ ገንዘቦች በመጠን መጨመራቸው ተስተውሏል።

በጥቁር ገበያው እየታየ ያለው የምንዛሪ ዋጋ ተመን መጨመርና በሕገወጥ የውጭ ምንዛሪ ዝውውር ከተያዙት ተጠርጣሪዎች በአንድ ጊዜ የተገኘው የውጭ ገንዘብ መጠን መጨመር መንግሥት ከፈቀደው የፍራንኮ ቫሉታ ንግድ ጋር ቀጥትኛ ግንኙነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ቢሆንም፣ የፍራንኮ ቫሉታ ንግድ አሠራር ጥንቃቄና ቁጥጥር ካልተደረገበት ይህንን መሰል ችግር ሊያመጣ እንደሚችል የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ይመክራሉ።

አንዳንድ ምግብ ነክ ምርቶችን በፍራንኮ ቫሉታ እንዲገቡ መፍቀዱ ተገቢ ቢሆንም፣ ይህ ውሳኔ በጥቁር ገበያውና በመደበኛው የውጭ ምንዛሪ ዋጋ መካከል ሰፊ ልዩነት እየፈጠረ ከሄደ በኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ ክምችት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳርፍ እንደሚችል ባሉሙያዎቹ ያነሳሉ።

በተለይ ፍራንኮ ቫሉታን ያላግባብ ትርጉም በመስጠት ከጥቁር ገበያ ዶላር በመግዛት ዕቃ ለማስመጣት የሚደረጉ ጥረቶች ከቀጠሉ፣ በሕጋዊ መንገድ ወደ አገር የሚገባ የውጭ ምንዛሪ እንዲቀንስ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ጭምር በጉዳዩ ዙሪያ አስተያየታቸውን የሰጡ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ገልጸዋል።

በዚህ ዙሪያ ማብራሪያ የሰጡት የማክሮ ኢኮኖሚ ባለሙያው ቴዎድሮስ መኮንን (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ በፍራንኮ ቫሉታ ምርትን ማስገባት የተለመደ አሠራር ቢሆንም፣ ከጥቁር ገበያ በተገዛ ዶላር ከሆነ፣ ፍራንኮ ቫሉታ የሚሰጠውን ጥቅም ከማዛባት ባለፈ ኢኮኖሚው ላይ ተፅዕኖ ያሳርፋል።

በመሆኑም ከጥቁር ገበያ የውጭ ምንዛሪ በመግዛት ዕቃ ለማስገባት የሚደረገው ሙከራ ቁጥጥር ሊደረግበትና በመደበኛው የምንዛሪ ዋጋና በጥቁር ገበያው መካከል ያለውን የምንዛሪ ዋጋ በጥብቅ መከታተል የሚሻ መሆኑንም አስረድተዋል።

እንደ ዶ/ር ቴዎድሮስ ገለጻ፣ ‹‹ሰዎች ፍራንኮ ቫሉታ ተፈቅዷል ሲባል፣ መጀመርያ የሚያደርጉት ወደ ጥቁር ገበያ በመሄድ የውጭ ምንዛሪ መግዛት ነው፤›› ይህ ፈፅሞ ትክክል ያለመሆኑን፣ ነገር ግን እየታየ ያለ ጉዳይ መሆኑ እንደሚያሳስባቸው አመልክተዋል። ምክንያቱም በፍራንኮ ቫሉታ ዕቃ ለማስመጣት ከጥቁር ገበያ የሚገዛው የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት እየጨመረ በሄደ ቁጥር በጥቁር ገበያ የምንዛሪ ዋጋው ከፍ ይላል። ስለዚህ በፍራንኮ ቫሉታ ዕቃ ለማስገባት ባልተገባ መንገድ የጥቁር ገበያው ዋጋ ከፍ እያለ መምጣት ደግሞ ከመደበኛው የምንዛሪ ዋጋ ጋር ያለውን ልዩነት እያሰፋው እንደሚሄድ ጠቁመዋል። የልዩነቱ መስፋት ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ችግር ሊያስከትል ይችላል የሚል ምልከታቸውን ቴዎድሮስ (ዶ/ር) አንፀባርቀዋል። በጥቁር ገበያውና በመደበኛው የውጭ ምንዛሪ ዋጋ መካከል የልዩነቱ መስፋት ከሚያስከትለው ችግር አንዱ ከውጭ በሕጋዊ መንገድ የሚገባውን የውጭ ምንዛሪ እንዲቀንስ ስለሚያደርግ ነው።

ምክንያቱም በጥቁር ገበያና በመደበኛው የምንዛሪ ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት ከሰፋ ከውጭ ገንዘብ የሚልኩ ሰዎች በጥቁር ገበያው ያለው ዋጋ ከፍ በማለቱ ዓይናቸውን ወደ ጥቁር ገበያው እንዲጥሉ የሚያስገድዳቸው መሆኑን ቴዎድሮስ (ዶ/ር) ገልጸዋል። ስለዚህ በመደበኛውና በጥቁር ገበያው መካከል ልዩነቱ እየሰፋ ከመጣ መንግሥት ይህንን ልዩነት ማቀራረብ ወይም የጥቁር ገበያው የምንዛሪ ዋጋ እንዲወርድ መውሰድ የሚገባውን ዕርምጃ መውሰድ እንዳለበት ይመክራሉ።

‹‹በጥቅል ሲታይ ፍራንኮ ቫሉታ በራሱ ምንም ችግር የሌለበት የፖሊሲ ውሳኔ አይደለም፤›› ያሉት ቴዎድሮስ (ዶ/ር)፣ ፍራንኮ ቫሉታ የቱንም ያህል ጠቃሚ ነው ቢባልም ውስብስብ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባም ተናግረዋል።

ሪፖርተር ያነጋገራቸው ሌላው የኢኮኖሚው ባለሙያ ለማ ጉዲሳ (ዶ/ር)፣ ‹‹ፍራንኮ ቫሉታ ያለ ውጭ ምንዛሪ ዕቃን ማስገባት እንጂ ለጥቁር ገበያ ዕውቅና መስጠት አይደለም። ነገር ግን ፍራንኮ ቫሉታ ማለት ጥቁር ገበያ ተፈቀደ ማለት ነው በሚል ወደ ጥቁር ገበያ መሄድ ትክክል አይደለም፤›› በማለት የቴዎድሮስ (ዶ/ር)ን ሐሳብ ይጋራሉ።

መንግሥት ፍራንኮ ቫሉታን ሲፈቅድ የውጭ ምንዛሪ ያላቸው አካላት የባንክ ፈቃድ ሳይጠየቁ ዕቃ ገዝተው ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላሉ በሚል እንጂ፣ ከጥቁር ገበያው ዶላር አይደለም። ይህ ከሆነ ግን ሕገወጥ ተግባር ነው፣ መንግሥትም የማይፈቅድ መሆኑን ለማ (ዶ/ር) ገልጸዋል። ይህ አካሄድ በመንግሥት ተቆጣጣሪነት ዕርምት እንደሚገባውም ሳያሳስቡ አላለፉም።

ከፍራንኮ ቫሉታ ጋር በተያያዘ ሌላም አሳሳቢ ችግር እንዳለ የጠቆሙት ለማ (ዶ/ር)፣ ይህም ከሕገወጥ የኮንትሮባንድ ንግድ ጋር የተያያዘ ነው። ሕገወጥ የኮንትሮባንድ ንግድ ከሌላው ጊዜ በተለየ ቁጥጥር የማይደረግበት ከሆነም ኢኮኖሚያዊ ችግር ያስከትላል ይላሉ። ፍራንኮ ቫሉታ ሕገወጥ የኮንትሮባንድ ንግድ እንዲስፋፋ ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፣ በሕገወጥ የኮንትሮባንድ ንግድ ላይ መደረግ ያለበት ቁጥጥር ጠንከር ሊል ይገባል።

እንደ ወርቅ፣ ቡና፣ የቀንድ ከብትና የመሳሰሉትን የወጪ ንግድ ምርቶች በመላክ የተሰማሩ ◈ ነ ጋ ዴ ዎ ች ና ሌሎችም ምርቶቹን በሕገወጥ መንገድ (በኮንትሮባንድ) በማስወጣት የሚያገኙትን የውጭ ምንዛሪ ደግሞ የተፈቀደውን የፍራንኮ ቫሉታ ዕድል ተጠቅመው ምርቶችን ለማስገባት እንዲሳቡ ያደርጋል። በመሆኑም ፍራንኮ ቫሉታ ጥንቃቄ

## ለግሉ ዘርፍ እድገት የሚሆን የ25



በኢትዮጵያ ለግሉ ዘርፍ እድገት የ25 ሚሊየን ዩሮ ፕሮጀክት የማስጀመሪያ ወርክሾፕ በአዲስ አበባ ተካሄደ ።

ፕሮጀክቱ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና በጀርመን ዓለም ዐቀፍ የልማት ትብብር ድርጅት (ጂአይዜድ) የተዘጋጀ ሲሆን ለ4 ዓመታት የሚቆይና ከሚያዝያ ወር ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚሆን ታውቋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ ሺሰማ ገብረሥላሴ የግሉ ዘርፍ በድህነት ቅነሳ ፈጣን እድገት ለማስመዝገብ እየተደረገ ባለው ሀገራዊ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ተናግረዋል።

የጀርመን መንግሥት በጂአይዜድ በኩል ለግሉ ዘርፍ እድገት ላለፉት ስድስት ዓመታት ድጋፍ በማድረግ ላይ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በተለይም የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪዎች አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ጥበቃን መሠረት ያደረገ ደረጃ እንዲኖራቸው በሥራ እድል ፈጠራና በኢንቨስትመንት ትልቅ ሚና እየተጫወተ ነው ብለዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ባይሳ በዳዳን ጨምሮ የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ የጀርመን ኤምባሲና የጂአይዜድ ኃላፊዎች መገኘታቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

ለተጨማሪ መረጃ፡ ◈

https://waltainfo.com/am/ለግሉ-ዘርፍ-እድገት-የሚሆን-የ25-ሚሊየን-ዩሮ/

## የአየር መንገዱ የጥገና ክፍል የመንገደኛ አውሮፕላንን ሙሉ በሙሉ ወደ እቃ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የአውሮፕላን ጥገና ክፍሉ ከእስራኤል ኤሮስፔስ ኢንደስትሪስ (IAI) ጋር በጥምረት በይንግ 767 የመንገደኛ አውሮፕላንን ሙሉ በሙሉ ወደ እቃ ጫኝ አውሮፕላን የመቀየር ስራ በተሳካ ሁኔታ ማገባደዱን አስታወቀ።

ዓየር መንገዱ ስኬታማ ክንውን ያለውን ይህንን ስራ አስመልክቶ እስካሁን ስለተገኘው ውጤት ማብራሪያ የተሰጠበት መርሃ ግብርንም አከናውኗል።

በቀጣይ ሁለት ወራት አውሮፕላኑን ሙሉ በሙሉ ወደ እቃ ጫኝ የመቀየሩ ተግባር ሲጠናቀቅ የአየር መንገድ የጥገና ክፍል በአፍሪካ ደረጃ የመንገደኛ አውሮፕላንን ሙሉ በሙሉ ወደ እቃ ጫኝነት አውሮፕላን የቀየረ የመጀመሪያው የጥገና ማዕከል እንደሚያደርገው ነው የተገለፀው።

በመርሃ ግብሩ ላይ በኢትዮጵያ የእስራኤልአምባሳደር አለልኝ አድማሱ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ጣሰው እና ሌሎች ተጋባዥ እንግዶች መገኘታቸውን ከዓየር መንገዱ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

ለተጨማሪ መረጃ፡ ◈

https://www.fanabc.com/የኢትዮጵያ-አየር-መንገድ-የጥገና-ክፍል-በ/

# የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ክለሳ ረቂቅ



የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ኢትዮጵያ ካዘጋጀችው የአሥር ዓመታት የልማት ዕቅድ ጋር አጣጥሞ ለማስኬድ እንዲቻል፣ ከዚህ ቀደም የነበረውን የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ክለሳ አድርጎ ረቂቁን እንዳጠናቀቀ አስታወቀ።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከዚህ ቀድሞ የነበረው የዘርፉ ፖሊሲ የነበረበት ችግር ወይም ጉደለት ምንድነው የሚለውን ዝርዝር እንደሠራ በማስታወቅ፣ ከአሥር ዓመት የልማት ዕቅዱ ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ የመነሻ ጥናት ወይም ረቂቅ ተዘጋጅቶ በዘርፉ ዕውቀት አላቸው ለሚባሉና ዘርፍን ሲመሩ ለቆዩ አካላትና የዩኒቨርሲቲ ምሁራን አቅርቦ አስተያየት እንደተሰጠበት፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ደኤታ አቶ ሺሰማ ገብረ ሥላሴ ለሪፖርተር ተናግረዋል።

የኢንዱስትሪ ስትራቴጂ ክለሳ ሥራው በአፍሪካ ልማት ባንክ ድጋፍ፣ ዳልበርግ የተባለ የውጭ አማካሪ ድርጅት ተቀጥሮ የጥናት ሥራውን እንደሠራው ከዚህ በፊት መገለጹ ይታወሳል።

የፖሊሲ ክለሳውን ማድረግ በዋናነት ማድረግ ካስፈለገባቸው ዋነኛ ምክንያቶች ውስጥ፣ ከዚህ ቀደም በአገልግሎትም ሆነ በኮንስትራክሽንና የንግድ ዘርፎች የተሰማሩ አካላት እንዴት ወደ አምራች ዘርፉ መሸጋገር ይችላሉ በሚለው ላይ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ታሳቢ ማድረግ አንዱ እንደሆነ ሚኒስትር ደኤታው አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል ከግብርና ዘርፉም ሀብት እየፈጠሩ ወደ ተቀናጀ አግሮ ፕሮሰሲንግ የሚገቡ አካላት ብቻቸውን ሳይሆን፣ በዙሪያቸው ከሚገኙ የገጠር የትራንስፎርሜሽን ማዕከላት ጋር ተመጋግበው ኢንዱስትሪውን የሚያሳድጉበትን ሁኔታ እንዲፈጠር የሚያስችል እንደሆነ ተመላክቷል። ረቂቅ ፖሊሲው በመጠናቀቁ በቀጣይ ወደ ውይይትና ውሳኔ ወደ የሚያሳልፈው የመንግሥት አካል በሚሸጋገርበት ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አቶ ሺሰማ ገልጸዋል።

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ የልማት ስትራቴጂ ከተዘጋጀበት ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ ባሉት 19 ዓመታት በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ብዙ ለውጦች በመኖራቸው ምክንያት፣ ዘርፉ ከአዳዲስ ሁኔታዎች ጋር የተጣጣመና እንዲሆን ታስቦ ፖሊሲው እንደተሻሻለ ተገልጿል።

ዋና ተዋናይ ከሆኑት የኢንዱስትሪ መሪዎችና ከተለያዩ የመንግሥት አካላት ጋር ውይይት ከተደረገበት በኋላ የሚፀድቅ እንደሆነ ያስታወቁት አቶ ሺሰማ፣ የፖሊሲ ክለሳው በዚህ ወቅት በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቶ መጠናቀቁን አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ካለፈው ጥር ወር ጀምሮ በይፋ የተሰረዘችበትን ከአሜሪካ መንግሥት የተሰጣታትን የንግድ ተጠቃሚነት ዕድል (አጎዋ) ለማስቀጥል፣ መንግሥት ከአሜሪካ ጋር ያለውን ግንኙነት የማሻሻል ሥራዎች እየሠራ እንደሚገኝ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታውቋል።

የኢትዮጵያ ከተጠቃሚነት ዕድሉ መሰረዝ ከሁሉም በላይ መንግሥት ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም ገበያ (በዩሮ ቦንድ) አንድ ቢሊዮን ዶላር የዕዳ ሰነድ ለሽያጭ በማቅረብ የሰበሰበውን የውጭ ምንዛሪ ካፒታል፣ እንዲሁም ከዓለም ባንክ ያገኛቸውን ብድሮች በመጠቀም በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች በገነባቸው ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ በሚገኙ የውጭ ባለሀብቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ሲገለጽ ቆይቷል።

በተለይም ግንባታቸው ተጠናቆ ወደ ምርት ተግባር ከተሸጋገሩት፣ እንዲሁም ብዙኃኑ በጨርቃ ጨርቅ ምርቶች ላይ የተሰማሩና የምርታቸው መዳረሻ ወደ አሜሪካ ያደረጉ ኩባንያዎች ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ ለአንዳንድ ድርጅቶች መዘጋት፣ በተጨማሪም ለሠራተኞች መበተን ምክንያት እንደሆነ እየተገለጸ ነው።

# የዓለም ገንዘብ ድርጅት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ

ባለፈው የጥቅምት ወር በየሁለት ዓመቱ በሚያወጣው የዓለም ኢኮኖሚ ምልከታ ሪፖርት የኢትዮጵያን የአገር ውስጥ ምርት ዕድገት (ጂዲፒ) ትንበያ ሳያካትት ያለፈው የዓለም የገንዘብ ድርጅት (አይኤምኤፍ)፣ በቀጣዮቹ ሁለት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የሚያንሰራራበት ዕድል መኖሩን አስታወቀ።

አይኤምኤፍ የሩሲያና የዩክሬይን ጦርነት የዓለምን ኢኮኖሚያዊ ማገገም ወደኋላ እንደሚመልሰው በብራራበት አዲሱ ሪፖርት፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እ.ኤ.አ በ2022 በ3.8 በመቶ ያድጋል ሲል ተንብዮ፣ በመጪው ዓመት ደግሞ ይህ ቁጥር ወደ 5.7 በመቶ ከፍ ይላል ብሏል።

በጥቅምት ወር ይፋ ተድርጎ በነበረው የድርጅቱ ትንበያ ላይ ኢትዮጵያን ጨምሮ አፍጋኒስታን፣ ሊባኖስ፣ ሊቢያና ሶሪያ የተያዘውን የአውሮፓውያን ዓመት ጨምሮ ለቀጣይ አምስት ዓመታት ባለው ጊዜ ውስጥ የሚኖራቸውን አጠቃላይ አገራዊ ምርት ዕድገት መተንበይ አለመቻሉን አስታውቆ ነበር።

ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገሮች ኢኮኖሚ በዋናነት የኮሮና ወረርሽኝ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከመከሰቱ ጋር ተያይዞ በተፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ ሳቢያ፣ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ማሽቆልቆል እንደሚገጥማቸው መተንበዩ አይዘነጋም። ኢትዮጵያ በትንበያው ያልተካተተችው በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ሳቢያ አገራዊ የምርት ዕድገት ሒደቱን ማመላከት አዳጋች ሆኖ በመገኘቱ እንደሆነ መግለጹ ይታወሳል።

ባለፈው ሳምንት ይፋ በተደረገው ሪፖርት በኢትዮጵያ ያለው የዋጋ ንረት እ.ኤ.አ በ2021 ከነበረበት 26.8 በመቶ ወደ 34.5 በመቶ እንደሚያድግ የተተነበየ ሲሆን፣ ነገር ግን ይህ አኃዝ እ.ኤ.አ በ2023 ወደ 30.5 በመቶ ዝቅ የማለት ዕድል አለው ተብሏል።

የሩሲያና የዩክሬይን ጦርነት የዓለም ምጣኔ ሀብትን እ.ኤ.አ በ2021 ከነበረው 6.1 በመቶ ዕድገት በ2022 ወደ 3.6 በመቶ ሊያወርደው እንደሚችል በሪፖርቱ ተመላክቷል። ይህ ደግሞ ጦርነቱ የውጪ ንግድ እንቅስቃሴዎችን በማስተጓጎል፣ የነዳጅና የምግብ ዋጋ ንረት በማስከተሉ እንደሆነ ሪፖርቱ ያሳያል።

ከሰሃራ በታች የሚገኙት ነዳጅ አቅራቢ አገሮች በአማካይ 3.4 በመቶ እንደሚያድጉ የተተነበየ ሲሆን፣ መካከለኛ ገቢ እንዳላቸው የሚነገርላቸው የአፍሪካ አገሮች ደግሞ በአማካይ 3.3 በመቶ እንደሚያድጉ ይጠበቃል።

ዝቅተኛ ኢኮኖሚ አላቸው የተባሉት አገሮች በአማካይ ሊያድጉ ይችላሉ የተባለበት አኃዝ 4.8 በመቶ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ 6.4 በመቶ፣ ኬንያ 5.7 በመቶ፣ ቡርኪናፋሶ፣ ታንዛኒያና ኡጋንዳ እንደ ቅደም ተከተላቸው ከ4.7 እስከ 4.9 በመቶ የሚመዘገብ ዕድገት እንደሚስመዘግቡ ሲጠበቅ፣ ኢትዮጵያ ደግሞ 3.8 በመቶ እንደምታድግ በሪፖርቱ ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ዕድገት የዝቅተኛ ገቢ አላቸው ተብሎ ከተቀመጡት የአፍሪካ አገሮች ዝቅ ብሎ ቢገኝም፣ የነዳጅ ላኪ አገሮች ዝርዝር ውስጥ ከሚገኙት ናይጄሪያ፣ አንጎላና ጋቦን፣ እንዲሁም መካከለኛ ገቢ ካላቸው እንደ ደቡብ አፍሪካና ዘምቢያ ከመሳሰሉ አገሮች ብልጫ እንዳለው የአይኤምኤፍ ሪፖርት ትንበያ ያሳያል።

# ባንኮች ዕዳቸውን መክፈል ባልቻሉ ሆቴሎች ላይ ለጊዜው ሐራጅ

ዕዳቸውን መክፈል ባልቻሉ ሆቴሎች ላይ ባንኮች የሚያወጡት ሐራጅ ለጊዜው እንዲያቆሙ፣ የኢትዮጵያ ሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪዎች አሠሪዎች ፌደሬሽን ጠየቀ።

የኮሮና ወረርሽኝ ከተከሰተ ጀምሮ በአገልግሎት ዘርፉ ላይ በደረሰው ጉዳት ሳቢያ፣ ሆቴሎች ከነበረባቸው መደበኛ ብድር በተጨማሪ ለድጋፍ የሚሆን ብድር በአነስተኛ ወለድ መውሰዳቸው ይታወሳል። አብዛኞቹ ሆቴሎችም መደበኛ ብድሮች ያሉባቸው ሲሆን፣ በተለይም ከኮሮና ወረርሽኝ በተጨማሪ በጦርነቱ ምክንያት የገበያ መቀዛቀዝን ጨምሮ ውድመት የደረሰባቸው ሆቴሎችም መኖራቸው ታውቋል።

በዚህም ምክንያት ሆቴሎች ያለባቸውን የባንክ ዕዳ መክፈል እንደማይችሉና በኮሮና ወረርሽኝ ሳቢያ የተበደሩት ገንዘብ እስከ አምስት ዓመት፣ እንዲሁም መደበኛ ብድሮች እስከ 20 ዓመት እንዲራዘምላቸው በተደጋጋሚ ቢጠይቁም ምላሽ አለማግኘታቸውን የሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪዎች አሠሪዎች ፌደሬሽን ፕሬዚዳንት ፍትሕ ወልደሰንበት (ዶ/ር) ለሪፖርተር ገልጸዋል።

ለብሔራዊ ባንክ ያቀረቡት የኮሮና ወረርሽኝ ወቅት ብድር መክፈያ ጊዜ ማራዘሚያ ውድቅ የተደረገ ሲሆን፣ የመደበኛ ብድሩ ማራዘሚያም ተቀባይነት አለማግኘቱን፣ በተለይም በጦርነቱ ምክንያት በአዲስ አበባ ያሉትም ሆኑ በሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች ያሉ ሆቴሎች ተጎጂ ሆነዋል ብለዋል። የብድር ማራዘሚያ ጥያቄዎቹ ውድቅ ከተደረጉ በኋላ፣ ከቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር በመሆን ሆቴሎቹ በሚደገፉበት ሁኔታ ላይ እየሠሩ መሆኑን ፍትሕ (ዶ/ር) ገልጸዋል።

በሆቴሎቹ ላይ በተለይም በጦርነቱ ምክንያት የደረሰውን ጉዳት ለይተው እንዲያቀርቡ በተሰጣቸው መመርያ መሠረት፣ ሁሉም የሆቴል ማኅበራት የጉዳቱን መጠን አጥንተው እንዲያቀርቡ እያደረጉ መሆኑን አብራርተዋል።

ነገር ግን ይህ ሥራ በሒደት ላይ እያለ ብድራቸውን ባልከፈሉ ሆቴሎች ላይ ባንኮች ሐራጅ እያወጡ መሆኑን ገልጸዋል። በመሆኑም ሆቴሎች የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እስኪያገኙና ወደ መክፈል አቅም እስኪመለሱ ድረስ፣ ባንኮች እንዲታገሱና ሐራጅ እንዳያወጡ ተጠይቀዋል ብለዋል።

# ከ3 ነጥብ 5 ቢሊየን ብር በላይ

የጉምሩክ ኮሚሽን በዘጠኝ ወራት ባደረገው ክትትል ከ3 ነጥብ 5 ቢሊየን ብር በላይ የሚያወጡ የኮንትሮባንድ እቃዎች በተለያዩ ቅርንጫፎች መያዛቸውን አስታወቀ።

ኮሚሽኑ በ9 ወራት ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ጋር በመቀናጀት ኮንትሮባንድን በመከላከል እና በመቆጣጠር ረገድ ያከናወናቸውን ሥራዎች በሚመለከት በቢሾፍቱ ከተማ ውይይት አድርጓል።

የጉምሩክ ኮሚሽን የህግ ተገዢነት ምክትል ኮሚሽነር አቶ ሙሉጌታ በየነ ፥ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ የአፈፃፀም ስልቱ ተለዋዋጭ እና በታጠቁ ኃይሎች ጭምር የሚፈጸም በመሆኑ ለቁጥጥር አስቸጋሪ እንዳደረገው ገልፀዋል።

በጉምሩክ ኮሚሽን የኢንተለጀንስ ዳይሬክተር አቶ ተገኔ ደረሰ ፥የጉምሩክ ኮሚሽን በዘጠኝ ወራት ባደረገው ክትትል ከ3 ነጥብ 5 ቢሊየን ብር በላይ የሚያወጡ የኮንትሮባንድ እቃዎች በተለያዩ ቅርንጫፎች መያዛቸውን ገልፀዋል።

በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የኮንትሮባንድ መከላከል ድንበር ቁጥጥር እና ትራንስፖርት ምክትል መምሪያ ኃላፊ ኮሚሽነር አይሻ ቶላ በበኩላቸው፥ ኮንትሮባንድን በመከላከል እና በመቆጣጠር ረገድ የነበረው ቅንጅታዊ ሥራ አበረታች መሆኑን ገልፀዋል።

የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ድርጊቱን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ኮሚሽነሩ መግለጻቸውን ከጉምሩክ

# አየር መንገዱ በኢትዮጵያና ቱርክ ንግድና



አየር መንገድ በኢትዮጵያና ቱርክ ንግድና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ላይ የጎላ ድርሻ እንዳለው አምባሳደር አደም መሃመድ ተናገሩ፡፡

በቱርክ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር አደም መሃመድ እና የቱርክ የሲቪል አቬሽን ተጠባባቂ ዳይሬክተር ጀነራል ከማል ዩከሴክ (ፐ/ር) ውይይት አድርገዋል፡፡

በውይይታቸው አምባሳደሩ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአፍሪካ ቀዳሚ አየር መንገድ መሆኑን በማንሳት ሁለቱ ሀገራት በንግድና ኢንቨስትመንት ዘርፍ የጎላ ድርሻ አለው ብለዋል፡፡

በሁለቱ አየር መንገዶች እ.ኤአ መስከረም 29/2021 የተፈረመው ስምምነትን ወደ ተግባር መቀየር አስፈላጊ በመሆኑ በሚቀጥለው ወር ወደ ኢትዮጵያ በመሄድ ከአቻቸው ጋር እንዲወያዩ ከማል ዬኩሱክን (ፐ/ር) ጠይቀዋል፡፡

አየር መንገዶቹ ትልቁን አውሮፕላን (wide body passenger) እና ካርጎ (cargo flights) በአዲስ አበባና በኢስታንቡል ለመጠቀም

# ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለሚገቡ ድርጅቶች ተጨማሪ

ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች መግባት ለሚፈልጉ የአገር ውስጥ ድርጅቶች ተጨማሪ ማበረታቻዎችን ለመስጠት ጥናት እየተደረገ መሆኑን፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በኢትዮጵያ ከሚገኙ 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች የውጭ ባለሀብቶች መሆናቸውን፣ ይህም ፓርኮቹ ከተገነቡበት የአገር ውስጥ አምራቾችን የማሳደግ ዓላማ አንፃር ውጤታማ እንዳልሆነ የሚያሳይ መሆኑን በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ዳይሬክተር አቶ አያልነህ አባዋ ለሪፖርተር ተናግረዋል፡፡

የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በተለይም ማሽነሪዎችን ማስገባት የሚችሉበት ማበረታቻ በአግባቡ ተግባራዊ እየተደረገ አይደለም የሚሉት ዳይሬክተሩ፣ ማሽነሪዎችን ከውጭ ለማስመጣት ጥያቄ አቅርበው ከሁለት ዓመታት በላይ የጠበቁና ምላሽ ያላገኙ ድርጅቶች መኖራቸውን አክለዋል፡፡ በተጨማሪም ብድር አግኝተው ወደ ሥራ ለመግባትም እንደሚቸገሩ ገልጸው፣ ለዚህም የባንኮች የብድር አሰጣጥ ሒደት በርካታ መሥፈርቶች የሚጠየቁበት መሆኑ ዋነኛው ምክንያት ነው ብለዋል፡፡

የኢኬቲ ትሬዲንግ ፕሮጀክት ማኔጀር አቶ አሰፋ አያሌው በበኩላቸው፣ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ለመግባት በተደጋጋሚ ጥያቄ ሲያቀርቡ እንደነበርና ምላሽ እንዳላገኙ ገልጸዋል፡፡ ቦታ ከማግኘት ጀምሮ ያሉት ሒደቶች ቀላል አለመሆናቸውንና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ማበረታቻዎች አለመኖራቸውን ተናግረዋል፡፡

በዚህም ምክንያት ወደ ኢንዱስትሪያል ፓርክ ለመግባት የነበራቸውን ፍላጎት በመተው፣ በነበራቸው ፋብሪካ ላይ ማስፋፊያ ማድረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገቡ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ከፍተኛ ውድድር የሚጠበቅባቸው በመሆኑና በማምረት ዘርፍ ያላቸው ልምድ አነስተኛ ስለሚሆን ፈታኝ እንደሚሆንባቸው የሚገልጹት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ያሬድ ኃይለ መስቀል፣ ለዚህም ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው አስረድተዋል፡፡

በኢትዮጵያ በአብዛኛው ከማምረት ይልቅ በንግድ ዘርፍ የመሰማራት ልምድ እንዳለ ገልጸው፣ በተለይ የማምረቻ ዘርፉ የሚጠይቀውን በረዥም ጊዜ የሚገኝ ትርፍ አውቆ መግባት ላይ ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ግንዛቤ ሊፈጠርላቸውና እንዲበረታቱም ጥቅማ ጥቅሞች ሊሰጧቸው ይገባል ይላሉ፡፡ የውጭ ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሲመጡ የራሳቸውን ማሽነሪዎች ማምጣት ስለሚችሉ በቀላሉ ወደ ሥራ እንደሚገቡ፣ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ግን እነዚህን የካፒታል ዕቃዎች በቀላሉ ማስገባት አለመቻላቸው አስቸጋሪ እንደሚያደርግባቸው አክለዋል፡፡

ወደ ማምረት የመግባት ልምድ ያላቸውም ቢሆኑ ያመረቱትን መሸጥ የሚችሉበት ገበያ ለማግኘት እንደሚቸገሩ ገልጸው፣ በተለይ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚመረቱ ምርቶች ለውጭ ገበያ ብቻ እንዲቀርቡ ከማድረግ ይልቅ ለአገር ውስጥ ገበያ በማቅረብ የሚነሳባቸውን የጥራትና ተወዳዳሪነት ችግር እንዲፈቱ ማስቻል ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የአገር ውስጥ ባለሀብቶቹ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች እንዳይገቡ የሚያደርጓቸውን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ለማሻሻልና አዳዲስ ማበረታቻዎችን ተግባራዊ ለማድረግ፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጥናት እያደረገ መሆኑን አቶ አያልነህ ተናግረዋል፡፡

# የግሉን ዘርፍ በተመለከተ የወጡ ሕጎችን የሚያስፈጽሙ ተቋማት አቅም ሊጎለብት

የግሉ ዘርፍ በስፋት የተሰማራባቸው የመካካለኛና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም ጀማሪ የሥራ ፈጣሪዎችን አስመልክተው የወጡ ሕጎች ወደ ተግባር እንዲቀየሩ፣ የአስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች አቅም ሊጎለብት እንደሚገባ ተገለጸ፡፡

ይህ የተገለጸው የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን ጨምሮ የጀርመን የፌዴራል ኢኮኖሚ ትብብርና ዕድገት ሚኒስቴር ፈጻሚ የሆነው የጀርመን ዓለም አቀፍ የልማት ትብብር ድርጅት (ጂአይዜድ) የግሉ ዘርፍ ዕድገት በኢትዮጵያ (Private Sector Development in Ethiopia(PSD-E) በሚል ከዚህ ቀደም ስምምነት የተደረገበትን ፕሮጀክት በይፋ ወደ ሥራ ባስገቡበት ወቅት ነው፡፡

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ የአገሪቱን ኢኮኖሚ በሚሸከምበት ደረጃ እንዲደርስ የግሉ ዘርፍ ሚናው ጉልህ በመሆኑ ለዘርፉ ዕድገትም ሆነ የዕቅድ አፈጻጸም ስኬት የተደላደለ የቢዝነስ አመቺነት ሊፈጠርለት እንደሚገባ በራዲሰን ብሉ ሆቴል ይፋ በተደረገው የፕሮጀክት ማስጀመሪያ አውደ ጥናት ላይ ተጠቅሷል፡፡

በጀርመን መንግሥት የኢኮኖሚ ትብብር ልማት ሚኒስቴር የፋይናስ ድጋፍ የሚደረግለት ይህ ፕሮጀክት አዲስ አበባን ጨምሮ በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ብሔርና ብሔረሰቦች፣ በሐረሪና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር እስከ መስከረም 2017 ዓ.ም. ተግባራዊ እንደሚደረግ ታውቋል፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ሺሰማ ገብረ ሥላሴ እንደተናገሩት፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የግሉ ዘርፍ አስተዋጽኦ የተሻለ እንዲሆን የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን ጠቅሰው፣ በተለይም የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን ተወዳዳሪነት ለማሻሻል ሥራዎች እየተሠሩ ነው ብለዋል፡፡

አገሪቱ በዚህ ወቅትም ሆነ በቀጣዮቹ ዓመታት በምትተገብረው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አውራ አንቀሳቃሹ የግሉ ዘርፍ እንደሚሆን የተናገሩት ሚንስትር ዴኤታው፣ በዚህም የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተግባር ተኮር ፖሊሲ መሠረት አድርጎ የቴክኖሎጂ ለውጦች ከግንዛቤ የከተተ፣ ምርታማነትን የሚያሳድግ፣ የግሉን ዘርፍ የሚያበረታታ እንዲሁም በገበያ ውስጥ የሚገጥመውን የገበያ እጥረት ችግሮች በመፍታት ረገድ ሚና ይኖረዋል ብለዋል፡፡

በፓናል ውይይቱ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም እንዳስታወቁት፣ የተቃዱና የታሰቡ ፕሮጀክቶች በተወጡነት ልክ ተግባራዊ እንዲሆኑ ከተፈለገ የቢሮክራሲ ውጣውረዶችን ማስወገድ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

በጂአይዜድ የግል ዘርፍ ልማት ኃላፊ የሆኑት ወ/ሮ አረጋሽ አስፋው ለሪፖርተር እንደተናገሩት፣ ጂአይዜድ ጀማሪ የሥራ ፈጣሪዎችን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን በቀጥታ ሳይሆን የሚደግፈው እነዚህን አካላት የሚያግዙትን መንግሥታዊ ተቋማትን አቅም በማጠናከር ነው፡፡

‹‹ሁል ጊዜ በዕርዳታ ድርጅት ድጋፍ በመደገፍ ሳይሆን ያለውን መዋቅር በምን ዓይነት ሁኔታ በማጠናከር ወደ ፊት መቀጠል ይቻላል?›› የሚለውን ድርጅቱ የሚደግፍ እንደሆነ የተናገሩት ኃላፊዋ፣ ጀማሪ የሥራ ፈጣሪዎችን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን የሚደግፉትን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የሳይንስና ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አቅም የማጎልበት ሥራ በፕሮጀክቱ የሚሠራ ቁልፍ ተግባር ነው ብለዋል፡፡

በአገሪቷ ከላይ የተጠቀሱትን ኢንዱስትሪዎችን የተመለከቱ በርካታ የወጡ ሕጎች እንዳሉ ያስታወሱት ወ/ሮ አረጋሽ፣ ለአብነትም የአሥር ዓመታት መሪ የልማት ዕቅዱ፣ የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው ተጠቃሾቹ ናቸው፡፡ ነገር ግን በእነዚህ ላይ የሰፈሩት ጉዳዮች ምን ያህል ወደ ታች ወርደው እየተሠራባቸው ይገኛሉ? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡በመሆኑም ይህንን ጥያቄ በመመለስ ሒደት ውስጥ አስፈጻሚ የሆኑትን የመንግሥት ተቋማት አቅም የማጠናከር ሥራ የሚሠራ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

ከዚህ በሻገር ኢንዱስትሪዎቹንና የሰው ኃይሉን በተመለከተ የአገናኝነት ሚና ያላቸውን በተለምዶ ኢንኩቤተሮች፣ አክስለሬተሮች የሚባሉትን ተቋማት በዓለም አቀፍ ደረጃ ልክ የሚያድጉበትንና እነሱም ለጀማሪ የሥራ ፈጣሪዎች በሥልጠና መልክ ትምህርት የሚሰጡበትን መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት የፕሮጀክቱ ግብ እንደሆነ ወ/ሮ አረጋሽ አስረድተዋል፡፡

ካለፈው ዘጠኝ ወር አንስቶ ፕሮጀክቱ በዝግጅት ምዕራፍ ላይ እንደቆየ የተናገሩት ወ/ሮ አረጋሽ፣ ከዚህ በኋላ ለፕሮጀክቱ በተመለመሉት ዓለም አቀፍ ኤክስፐርቶች አማካኝነት የተግባር ሥራውን የሚጀምር ይሆናል ብለዋል፡፡

# የአበባ አምራቾች ይፈቱልን የሚሏቸው ሁለቱ

በአሁኑ ወቅት ዋና ዋና ከሚባሉ የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ ምርቶች መካከል አንዱ የሆነው አበባ በመንግሥት እየወጡ ያሉ መመርያዎች ዘርፉ ላይ ተፅዕኖ እያሳረፉ እንደሆነ እየተገለጸ ነው።

ከዘርፉ ተዋንያኖች እየተሰማ እንዳለው በቅርቡ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወጣው የአበባ የወጪ ንግድ የመሸጫ ዝቅተኛ ዋጋ ወለልና የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀምን የሚመለከቱት መመርያዎች በዋናነት ተጠቅሰዋል።

በተለይ የአበባ የወጪ ንግድና የዋጋ ተመንን በተመለከተ የኢትዮጰያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመርያ አሁን ባለበት ደረጃ መተግበር የለበትም በሚል የኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ አምራችና ላኪዎች ማኅበር አቤት ብሏል።

ተግባራዊ እንዳሆን በወጣው መመርያ መሠረት ኤክስፖርት ማድረግ አስቸጋሪ መሆኑን በመግለጽ መመርያው ይሻሻል ዘንድ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን ለግብርና ሚኒስቴር ይህንኑ ቅሬታ ያገናዘበ አቤቱታውን ማኅበሩ እንዳቀረበ ታውቋል።

ማኅበሩ በአበባ የወጪ ንግድ አዲሱ የዋጋ ተመን ላይ ያለውን ቅሬታና ሊያስከትል የሚችለውን ችግር በዝርዝር ቢያቀርብም፣ አሁን ባለው ሁኔታ ጉዳዩን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየተነጋገረበት ከመሆኑ ውጪ ለጊዜው ተጨማሪ ማብራሪያ ከመስጠት ተቆጥበዋል።

በአዲሱ መመርያ መሠረት አበባ ላኪዎች ከዚህ በኋላ የሚልኩበት የዋጋ መጠን በአማካይ 4.66 ዶላር እንደሆነ የተወሰነ ሲሆን፣ ይህም ቀድሞ ከነበረው ዋጋ በ66 የአሜሪካን ሳንቲም ጭማሪ ያሳየ ነው። ይህ መመርያ እንዲተገበር ጥናቱን አዘጋጅቶ ለብሔራዊ ባንክ ያቀረበው የግብርና ሚኒስቴር ሲሆን፣ ማኅበሩም ሆነ የዘርፉ ተዋናዮች ግብርና ሚኒስቴር ጥናቱን በበቂ ሁኔታ አሰናድቷል የሚል እምነት የላቸውም። በዚህ መመርያ ቅሬታ ያላቸው አበባ ላኪዎች ለግብርና ሚኒስቴር እና ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያላቸውን ቅሬታ አቅርበው በጉዳዩ ላይ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በግንባር ሲነጋገሩበት መሰንበታቸው የታወቀ ሲሆን፣ ከዚህም በኋላ በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ምክክር ያደርጋሉ ተብሎ እየጠበቀ ነው።

በኢትዮጵያ የአበባ ኢንቨስትመንት ውስጥ ከፍተኛ የገበያ ድርሻ እንዳለው የሚነገርለት የዝዋይ ሮዝ ፕሮዳክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ኃላፊ አቶ ኤርሚያስ ሰለሞን ለሪፖርተር እንደገለጹት ደግሞ፣ በአሁኑ ጊዜ በዘርፉ ውስጥ ካሉ ዋና ዋና ችግሮች መካለከል አንዱ በቅርቡ በብሔራዊ ባንክ ያወጣው ዝቅተኛ የዋጋ ተመንን የተመለከተው መመርያ ነው። ይህ መመርያ ዘርፉ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳርፍ እንደሚችል ጠቁመው፣ በተለይ መመርያው ወቅቱን ባላገናዘበ ሁኔታ መውጣቱን ጠቁመዋል።

የአበባ ምርት ኤክስፖርትን አሁን በወጣው ዋጋ መሠረት መተግበር አስቸጋሪ እንደሚሆን በመግለጽ፣ ብሔራዊ ባንክም ሆነ ግብርና ሚኒስቴር ይህን መመርያ ዳግም ሊያጤኑት ካልቻሉ አበባ ላኪዎችን ኪሳራ ላይ ሊጥል ይችላል የሚል ሥጋታቸውን ገልጸዋል።

አሁን ባለው ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ በአውሮፓ ያለው ገበያ በቀድሞው ልክ እየሄደ እየሄደ እንዳልሆነ፣ ወደ ሩሲያና ወደ ዩክሬን የሚላከው አበባ ከማዕቀብና ከገበያ ፍላጎት አንፃር ገበያው ችግር እንደገጠመው የሚናገሩት አቶ ኤርሚያስ፣ በዚህም ምክንያት የአበባ ዋጋ እንደወደቀና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሰሞኑ ባወጣው ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ ገበያ ማግኘት ፈጽሞ አስቸጋሪ እንደሚሆን ያስረዳሉ።

በመሆኑ መመርያው የወጣበት ወቅት ነባራዊውን ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ከግምት ያላስገባና ዓለም አቀፍ ገበያው እየሰጠ ያለው ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ ያላገናዘበ በመሆኑ መመርያው በድጋሚ ሊታይ እንደሚገባ አቶ ኤርሚያስ ይመክራሉ።

መመርያው የወጣው የአበባ ዋጋ ከፍተኛ በነበረበት ወቅት ቢሆን ኖሮ ችግር ላይኖረው እንደሚችል የሚገልጹት አቶ ኤርሚያስ፣ በሆላንድ ጨረታ ላይ በዜሮ ጭምር እየተወጣ ባለበት በአሁኑ ወቅት አበባው ከሚሸጥበት ዋጋ በላይ እንዲሸጥ የሚያስገድድ መመሪያ ማውጣት ተገቢ እንዳልሆነም ያሰምሩበታል።

ማኅበሩም ሆነ አቶ ኤርሚያስ በዚህ መመርያ አተገባበር ላይ በዋናነት የሚያቀርቡት ቅሬታ መመርያ ከመውጣቱ አስቀድሞ ባለድርሻ አካላት እንዲመክሩበት አለመደረጉ ነው። መመርያው ከወጣም በኋላ ቢሆን ባለድርሻ አካላትን ጠርቶ ማነጋገር ተገቢ እንደሆነ ይናገራሉ።

የግብርና ሚኒስቴርም ሆነ ብሔራዊ ባንክ አበባ ወደ ውጭ ሲላክ መገኘት የሚገባውን የውጭ ምንዛሪ መጠን ወይም ዋጋ በተመለከተ የተደረገው የጥናት ውጤት ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቢመክር ኖሮ የተሻለ ውጤት ይገኝ እንደነበር የዘርፉ ተዋናዮች ያምናሉ።

አሁንም ቢሆን በወጣው መመርያ ላይ ውይይት በማድረግ መፍትሔ የማይበጅ ከሆነ የአበባ የወጪ ንግድ ላይ ተፅዕኖ ከማሳረፉም በላይ የወጪ ንግድ ገቢውን እንደሚጎዳ ያሰስባሉ።

ከዚህ መመርያ ባሻገር አሁን ላይ ለአበባ ላኪዎች ትልቅ ተግዳሮት የሆነው ጉዳይ በብሔራዊ ባንክ ከወራት በፊት የወጣው ሌላ መመርያ ነው። ይህም ከውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የተተገበረው መመርያ ነው። በዚህ መመርያ መሠረት ላኪዎች ከሚያገኙት የውጭ ምንዛሪ መጠቀም የሚችሉት 20 በመቶን ብቻ መባሉ ነው። አቶ ኤርሚያስ እንደገለጹት፣ በዚህ መመርያ መሠረት አበባ ላኪዎች ከሚያገኙት የውጭ ምንዛሪ 20 በመቶውን ብቻ እንዲጠቀሙ መወሰኑ ኢንዱስትሪውን እንደሚጎዳ ይገልጻሉ። ከዚህ ቀደም በነበረው

# በአትክልትና ፍራፍሬ ኤክስፖርት መሸጫ ዋጋ ላይ የተደረገው ጭማሪ በጅቡቲ

የአትክልትና ፍራፍሬ ኤክስፖርት ዝቅተኛ መሸጫ ዋጋ ላይ ጭማሪ ከተደረገና ይህም ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ከ15 ቀናት በኋላ ተግባራዊነቱ ለተወሰነ ጊዜ እንዲዘገይ ተወሰነ።

ባመዛኙ ወደ ጎረቤት አገሮች ለዓብነትም ወደ ጅቡቲና ሶማሊያ እንዲሁም ወደ መካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ኤክክፖርት የሚደረጉ የአትክልትና ፍራፍሬ ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ ወለል ላይ የዋጋ ማስተካከያ ጭማሪ እንዲደረግ የግብርና ሚኒስቴር በመወሰን ይህንኑ ውሳኔውን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስታውቆ ነበር።

ብሔራዊ ባንክ በበኩሉ የግብርና ሚኒስቴርን ውሳኔ መነሻ በማድረግ ለሁሉም ባንኮች መጋቢት 16 ቀን ባስተላለፈው የሥራ መመሪያ አትክልትና ፍራፍሬ ላይ የተደረገውን የዋጋ ማስተካከያ አስታውቆ ነበር።

ብሔራዊ ባንክ ለሁሉም ባንኮች በሰጠው የሥራ መመሪያ አትክልትና ፍራፍሬ ኤክስፖርት ላይ የተደረገው ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ ማስተካከያ እ.ኤ.እ. ከኤፕሪል 1 ቀን 2022 ጀምሮ ወደ ትግበራ እንደሚገባ ጠቅሷል።

በመሆኑም ማንኛውም የአትክልትና ፍራፍሬ ኤክስፖርተር ከተሻሻለው ዝቅተኛ ዋጋ በታች መሸጥ እንደማይችል እንዲሁም ሁሉም ባንኮች ከተቀመጠው ዋጋ በታች የባንክ ፐርሚት መፍቀድ እንደማይችሉ አስታውቋል።

በመሆኑም የአትክልት፣ ፍራፍሬና ዕፀ ጣዕም ምርቶች በተስተካከለው ዝቅተኛ መሸጫ ዋጋ እ.ኤ.አ. ከ ኤፕሪል 1 ቀን ጀምሮ ኤክስፖርት መደረግ ከተጀመረ በኋላ የግብርና ሚንስቴር የዋጋ ማስተካከያው ተግባራዊነት ለተወሰነ ጊዜ እንዲዘገይ ወስኗል።

ግብርና ሚንስቴር ይህንኑ ውሳኔውን ለብሔራዊ ባንክ መጋቢት 29 ቀን 2014 ዓ.ም. በላከው ደብዳቤ አስታውቋል።

‹‹የዋጋ ማሻሻያው ትግበራ የሽግግር ጊዜ የሚያስፈልገው ሆኖ ስለተገኘ፣ የተሻሻለው ዋጋ ትግበራ እ.ኤ.አ. እስከ ሜይ 15 ቀን 2022 ድረስ እንዲዘገይ እንጠይቃለን፤›› ሲል በግብርና ሚኒስትሩ ኡመር ሁሴን ተፈርሞ የተላከው ደብዳቤ ላይ ምክንያቱ ተመላክቷል።

በዚሁ ጥያቄ መሠረት የኤክክፖርት ምርቶቹ ቀድሞ በነበረው ዝቅተኛ መሸጫ ዋጋ ኤክስፖርት የሚደረጉ ይሆናል።

እንደ ምንጮች ገለጻ አዲሱ የአትክልትና ፍራፍሬ የወጪ ንግድ ዋጋ በጂቡቲ በኩል ቅሬታ በማስነሳቱ ለስምንት ቀናት አትክልትና ፍራፍሬ ወደ ጂቡቲ ሳይላክ ቀርቷል።

በአዲሱ ዋጋ ላይ የጂቡቲ ንግድና ቱሪዝም ሚኒስቴር ያለውን ቅሬታ ጂቡቲ ለሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ አቅርቦ፣ ኤምባሲውም ጉዳዩ እንዲታይ ለኢትዮጵያ ግብርና ሚኒስቴር በደብዳቤ ማሳወቁና ይህ ደብዳቤ ከተጻፈ በኋላ ብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመሪያ ይዘግይ ለመባሉ ዋናው ምክንያት ይኸው የጂቡቲ ቅሬታ ሳይሆን እንዳልቀረ ታምኗል።

የጂቡቲ ንግድና ቱሪዝም ሚኒስቴር የዋጋ ማሻሻያው የጅቡቲን የመግዛት አቅም ከመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ጋር ያነፃፀረ መሆኑና የዋጋ ማሻሻያው ተግባራዊ መደረግ የተጀመረው የረመዳን ፆም በጀምርበት ወቅት መሆኑ ትክልል እንዳልሆነ በመጥቀስ፣ ቅሬታውን ለኢትዮጵያ መንግሥት እንዳስታወቀ ሪፖርተር ከተመለከታቸው የደብዳቤ ልውውጦች ለመረዳት ችሏል።

የጅቡቲ መንግሥት የዋጋ ጭምሪው ላይ ላነሳው ቅሬታ የጠቀሳቸው ሌሎች ምክንያቶች ደግሞ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ያስከተለው የኢኮኖሚ ጉዳትና በሩሲያና በዩክሬን ጦርነት ያስከትለው የዋጋ አለመረጋጋት ይጠቀሳሉ።

በተጠሱት ምክንያቶችና ጅቡቲ 80 በመቶ የሚሆነውን የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት የምታገኘው ከኢትዮጵያ መሆኑንና ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች የዋጋ ጭማሪው በጅቡቲ ላይ ተፈጻሚ እንዳይሆን የአገሪቱ መንግሥት መጠየቁን ለማወቅ ተችሏል።

በግብርና ሚኒስቴርም የዋጋ ጭማሪው ተግባራዊነት በአጠቃላይ እንዲዘገይ የወሰነውና ይህንንም ለብሔራዊ ባንክ ያስታወቀው ከዚህ የጂቡቲ ቅሬታ በኋላ መሆኑንም እየተገለጸ ነው።

የግብርና ሚኒስቴር የአትክልት፣ ፍራፍሬና ዕፀ ጣዕም የወጪ ንግድ ዋጋን ማሻሻል ያስፈለገው ባደረገው ጥናት መሠረት በጎረቤት አገሮችና መካከለኛው ምሥራቅ የፍጆታ ፍላጎትና የመግዛት አቅም ማደጉ ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋውን ለማሻሻል መሠረታዊ ምክንያት እንደሆነ ይገልጻል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

ዋና አዘጋጅ፡-

ደበበ አበበ

አዘጋጅ፡-

ዮሴፍ ተሾመ


አድራሻ፡-

ስልክ-፡- +251-115-54-09-93

ፋክስ፡-+251-011-5517699

ድረ-ገጽ፡-
www.ethiopianchamber.com

Facebook:
https://www.facebook.com/
EthiopianChamber

Twitter:
https://twitter.com/
EthiopiaChamber

Telegram:
t.me/ethiopiachamber


## ECCSA Resource Center

Ethiopian Chamber of Commerce & Sectoral Associations (ECCSA) Resource Center has stated giving service to member. The center is located at the head quarter of ECCSA.

It is a unit dedicated to serve the business community, its members and staffs with a range of timely and cost-effective information services which will enhance the decision-making process and competitiveness of the chamber system management and the business community.

It is also a WTO (World Trade Organization) Reference Center for the private sector, to enable business community to access online trade data and WTO-related documents on a continuous basis, to help identify market niches for the export of their products and services.

The center works on the principle of the 5Rs: providing the Right information to the Right person at the Right time in the Right quantity and Right quality.

The Center's Services

Reference, Resources Loan & Interlibrary Loan Services

Internet & Electronic Resource Services

Support on information searching

Reprographic Service

Advising users on reference materials available in resource center.

Types of Materials in the Center

Books, Periodicals, Journals, Magazines

Audio and Video CD collections

E-Books & Publications

Business & Economic Statistics & Databases

Access to international organization's online information (WTO, ITC, UNCTAD, World Bank, PACCI, WCO, etc.)

For further information:

Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations

ECCSA Resource & WTO Reference Center

## የግልግል አገልግሎት



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/95 አንቀጽ 5(6) መሰረት በንግድ ማህበረሰቡ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን እንዲፈታ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህም መሰረት አለመግባባቶችን በፈጣን እና ሚስጥራዊነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲፈታ ከማድረጉም በላይ ለባለ ጉዳዮች አመቺ እንዲሆን ቅዳሜንም ጨምሮ ዓመቱን ሙሉ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑን የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ እንድትሆኑ ስንጠይቅ የንግድ ማኅበረሰቡን ለማገልገል ያለንን ቁርጠኝነት በመግለጽ ነዉ፡፡

ለበለጠ መረጃ ፡- ሜክሲኮ አደባባይ በሚገኘዉ የንግድ ምክር ቤት
ሕንጻ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 15 በአካል በመቅረብ
ወይም
በስልክ ቁጥር +251 115 311015 በመደወል ማነጋገር ትችላላችሁ፡፡

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የግልግል ማዕከል